# አዲስ ዘመን

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 020 መስከረም 20 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ




ፎቶ፡- ሃይሽ አብርሃ

# ድምፃዊ ማዲንጎ አፈወርቅ
## ለአገር ሳይሰስቱ የማገልገል ተምሳሌት ነው

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ ለአገር ሳይሰስቱ የማገልገል ተምሳሌት እና እውነተኛ አገር ወዳድ እንደነበረ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ገለጹ። የተወዳጁ አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ ሥርዓተ ቀብር በትናንትናው ዕለት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈፅሟል።

የአርቲስቱ ሥርዓተ ሸኝት በወዳጅነት አደባባይ ሲፈፀም በስፍራው በመገኘት ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፤ ማዲንጎ በህልውና ዘመቻው ለአገሩ ክብር መጠበቅ የሰሰተው የለም፤ በሙያው ሰራዊቱን አጀግኗል ብለዋል።

አርቲስቱ አገሪቱ ፈተና ላይ በነበረችበት ወቅት በህልውና ዘመቻ ለአገሩ ክብር መጠበቅ ያልሰሰተና በሙያው ሰራዊቱን ያጀገነ ታላቅ ድምፃዊ ነው ሲሉም አክለዋል።

ከንቲባ አዳነች፤ ማዲንጎ ሰው አክባሪ፣ ለሙያው ታማኝ እና ደግ ነበር፤ ሞት ተፈጥሯዊ በመሆኑ ለነገ የሚጠቀስ መልካም ሥራ ሠርቶ ያለፈ፣ ሥሙ ከመቃብር


ድምፃዊ ማዲንጎ አፈወርቅ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ

# ኢትዮጵያውያን እየገጠሙን ያሉ ችግሮችን በቀደሙት የችግር መፍቻ መንገዶቻችን ልንፈታቸው ይገባል

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን ካሁን በፊት የገጠሟቸውን ችግሮች በመደጋገፍና በመተባበር እየፈቱ የመጡበትን ልምድ በማስቀጠል አሁንም እየገጠሙ ያሉ ችግሮቻቸውን በጋራ ሊፈቱበት እንደሚገባ የኢትዮጵያ የኃይማኖት አባቶች ገለጹ።

ምዕመኑ «ለወገን በመድረስ የእምነት ግዴታችንን እንወጣ!» በሚል እሳቤ በገንዘብ ሚኒስቴር በተከፈተው


ኢትዮጵያውያን እየገጠሙን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# ስግድያ ሲፈስጉ የነበሩት ባለሀብት በግንባር ተገኝተው ድጋፍ አደረጉ

ጌትነት ተስፋማርያም

ወይዘሮ ስንታየሁ ማሞ በደሴ ከተማ በአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ላይ የተሰማሩ ባለሀብት ናቸው። አሸባሪው ትህነግ በ2013 ዓ.ም የደሴን ከተማ በወረረበት ወቅት ታጣቂዎቹ የባለሀብቷን ፎቶ ይዞ ሲያፈላልጋቸው እንደነበር ያስረዳሉ። በወቅቱ የተሻለ ጥሪት ያላቸውን ግለሰቦች በማፈላለግ ላይ የተጠመዱት የሽብር ቡድን አባላት ያገኙትን ገንዘብ ይዘርፉ፤ ሲያሻቸውም ንጹሃኑን ይገድሉ እንደነበር ገልጸዋል።

የበርካቶችንንብረትየዘረፉትየሽብርቡድንታጣቂዎች የባለሀብቷን ንግድ ዕቃዎች ጭነው መውሰዳቸውንና መውሰድ ያልቻሉትንም ማበለሻታቸውን አስታውሰዋል። የእርሳቸውንም ፎቶ እያሳዩ የት ነው ያለችው በሚል ሲያፈላልጓቸው የነበረው ያላቸውን ገንዘብ ሁሉ ሊቀሙና ብሎም ሕይወታቸውን ሊቀጥፉ እንደነበር ተናግረዋል።

ግና እርሳቸው ይህን ጥፋት ቀድመው አውቀዋልና ንብረታቸው ቢወድምም ሕይወታቸውን ለማትረፍ አንድ ስፍራ ላይ ተሸሽገው በመቆየታቸው ሊያገኟቸው


ስግድያ ሲፈስጉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፡- ዳኜ አበራ



# ጀግና የሕዝብ ልጅ ነው ያጣነው
## - አርቲስቶች

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- ጀግና የሕዝብ ልጅ ነው ያጣነው ሲሉ አንጋፋና ወጣት አርቲስቶች ገለጹ። የድምፃዊ ማዲንጎ አፈወርቅ የቀብር ሥነ-ሥርዓት በትናንትናው ዕለት በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቤተክርስቲያን ተፈፅሟል።

በቀብር ሥርዓቱ ላይ የተገኙት አርቲስቶች ድምፃዊውን ጀግና አገሩን የሚወድ አገሩ በምትጠራው ጊዜ ሁሉ ፈጥኖ የሚደርስ ብለውታል። በመርህግብሩ


ጀግና የሕዝብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










ኢትዮጵያ

በመንግሥታቱ ድርጅት 77ኛው ጠቅላላ ጉባዔ ወሳኝ አቋሞቿን አስረድታለች

ገጽ 3



# የኢሬቻ በዓል በሰላም እንዲከበር ግብረኃይሉ ዝግጅቱን አጠናቋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢሬቻ በዓል በሰላም እንዲከበር አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት ማጠናቀቁን የፀጥታና ደህንነት ግብረኃይል አስታወቀ።

የፀጥታና ደህንነት ግብረኃይሉ ከአባገዳዎችና የአገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን የኢሬቻ በዓልን ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲከበር የተደረገውን ዝግጅት አስመልክቶ ትናንት ውይይት አድርጓል።

በውይይቱም የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጀኔራል ደመላሽ ገብረሚካኤል እንደተናገሩት፥ በዘንድሮ የኢሬቻ በዓል ከኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎችና ከጎረቤት አገር በርካታ እንግዶች ይታደማሉ።

የፀጥታና ደህንነት ግብረኃይሉም ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ሰፊ ዝግጅት ሲያደርግ መቆየቱንና ማጠናቀቁን ለአባገዳዎች አብራርተዋል።

በአጠቃላይ በዓሉ በሰላም እንዲከበር በሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ በቂ ዝግጅት መደረጉንም ኮሚሽነር ጀኔራል ደመላሽ ገልጸዋል።




# ኢትዮጵያ በፖሊስ ሥራ ልምዷን ለአገራቸው እንድታካፍል የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ጠየቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ለሶማሊያ ፌዴራል ሪፐብሊክ ፖሊስ ልምዱን በማካፈል እገዛ እንዲያደርግ የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሐሰን ሼክ ሞሃሙድ ጠየቁ። ፕሬዚዳንቱ በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ዋናው መስሪያ ቤት የሥራ ጉብኝት አድርገዋል።

ፕሬዚዳንቱ ከልዑካን ቡድናቸው ጋር በመሆን በተቋሙ ዋና መስሪያ ቤት ሲደርሱ በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ማኔጅመንት አባላት በፖሊሳዊ ሥነ-ሥርዓት ደማቅ አቀባበል ተደርጎላቸዋል።

የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ የታጠቃቸውን ዘመናዊ የቴክኖሎጂ አቅሞችን እና ተቋሙ አሁን የደረሰበትን የለውጥ ደረጃ ተዘዋውረው ጎብኝተዋል።

ፕሬዚዳንት ሐሰን ሼክ ሞሃሙድ በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ እየተከናወነ ባለው ሪፎርም መደሰታቸውንና ስለተመለከቱት የለውጥ ሥራም አድናቆታቸውን ገልጸዋል።

በቀጣይ የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ለሶማሊያ ፌዴራል ሪፐብሊክ ፖሊስ ልምዱን በማካፈል እገዛ እንዲያደርግም ጠይቀዋል።

ከጉብኝቱ በኋላም ከኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጀኔራል ደመላሽ ገብረሚካኤል ጋር የሁለቱን አገራት የፖሊስ ኃይል ለማጠናከር በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ተነጋግረዋል።

በኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ የሶማሊያ ፖሊስ ወጣት መኮንኖች ገብተው እንዲማሩና እንዲሰለጥኑ ፕሬዚዳንቱ ያቀረቡትን ጥያቄ ኮሚሽነር ጀኔራል ደመላሽ ገብረሚካኤል ተቀብለዋል።

ኮሚሽነሩ የሁለቱ አገራት የፖሊስ ተቋማት ጠንካራ የጋራ የፀጥታ ግብረ ኃይል አቋቁመው በድንበር አካባቢ የጋራ ጥበቃ ለማድረግ እና በሽብርተኝነት ላይ የተጀመረውን ዘመቻ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ መናገራቸውን ከፌዴራል ፖሊስ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።



# በአማራ ክልል በአሸባሪው ትህነግ የተፈጸሙ ግፎችንና ውድመቶችን የሚያጋልጥ ድረ-ገጽ ይፋ ሆነ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በአሸባሪው ትህነግ የተፈጸሙ ግፎችንና ውድመቶችን የሚያጋልጥ ድረ-ገጽ ይፋ ሆነ።

በአማራ ክልል የሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፎረም ዋና ጸሐፊ ዶክተር አስማረ ደጀን እንደተናገሩት፤ ድረ ገጹ በተለያዩ ጊዜያት የሽብር ቡድኑ የፈጸማቸውን የሰብዓዊ፣ የሥነ ልቦናና ቁሳዊ ጉዳቶችን ተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ ተቀምጧል።

ድረ ገጹ አሸባሪው ቡድኑን ለመደገፍ የሚያደርገውን ጥረት የዓለምአቀፉ ማህበረሰብ እንዲረዳና እንዲያውቅ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል ብለዋል።

የአማራ ምሁራን መማክርት ጉባኤ የቦርድ አባል ዶክተር ዮናስ ተስፋ በበኩላቸው፤ በጥናት የተገኙ ውጤቶችን የዓለምአቀፉ ማህበረሰብ እንዲያውቅ በድረ ገጽና በመጽሐፍ ተሰንደው ተቀምጠዋል ብለዋል። በጅዎስፓሻል ድረ ገጹ ውድመት፣ ሞትና ሰቆቃ ደረሰባቸው የተባሉ አካባቢዎችና የሰዎች ቁጥር በተጨባጭ ማስረጃዎች ተደግፎ ይገኛል።

ድረገጹ በአማራ ክልል በጦርነቱ የተጎዱ አካባቢዎች መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፈንድ ጽሕፈት ቤት፣ በአማራ ምሁራን መማክርት እና በአማራ ክልል ዩኒቨርሲቲዎች ፎረም በልጽጎ ጥቅም ላይ ውሏል።

በድረ ገጹ በጥናት የተለዩ የጉዳት መጠን ዝርዝሮች ተካትተዋል። በዚህም በአማራ ክልል አሸባሪው ትህነግ በፈጸመው ወረራ 292 ቢሊዮን ብር የሚገመት ንብረት ወድሟል፣ 240 ሺህ 236 ሰዎች ላይ የግድያ እንዲሁም ድብደባ ቀላልና ከባድ ጉዳት መድረሱን በወቅቱ ተገልጿል። ይህም በድረ ገጹ ሰፍሮ እንደሚገኝና የዓለምአቀፉ ማህበረሰብ የጉዳቱን መጠን እንዲረዳው የሚያስችል መሆኑ ተጠቅሷል።

# የወንዞች የፍሰት መጠን የሚለካበት ዘመናዊ ሥርዓት በያዝነው ዓመት ይዘረጋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ወንዞች የፍሰት መጠን መለኪያ ‹ቴሌ ሜትሪ› ሥርዓት እንደሚዘረጋ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ገለፀ።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ሃብታሙ ኢተፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ የኢትዮጵያ የወንዞች የፍሰት መጠን አለመታወቁ እና የውሃ ሀብት መረጃዎች በተበታተነ መልኩ መቀመጣቸው አገሪቱ የውሃ ሀብቷን በአግባቡ እንድትጠቀም እያስቻለ አይደለም። በመሆኑም በዘንድሮው ዓመት የወንዞችን የፍሰት መጠን በዘመናዊ መልኩ ለመለካት የሚያስችል ሥርዓት እና የንፁሕ መጠጥ ውሃ ሀብት መረጃዎችን ወደ አንድ ቋት የማስገባት ሥራዎች ይከናወናሉ።

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፣ ከዚህ በፊት ያለው የወንዞች ፍሰት መጠን በአካል ቦታው ላይ ሄዶ በመለካት የሚታወቅ ከመሆኑም ባሻገር ለአሠራር ምቹ ያልሆነ ነው። የወንዞች የፍሰት መጠን በዘመናዊ ሥርዓት መለካት አለመቻሉ ደግሞ በተለያዩ ወንዞች ተፋሰስ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎችን ሕይወት ለአደጋ ሲያጋልጥ ቆይቷል። ከዚህም ባሻገር የወንዞች የፍሰት መጠን በዘመናዊ መልኩ አለመታወቁ የሕዳሴው ግድብ እንዳይገነባ ለሚሹ አካላት የክስ ምንጭ ሆኖ ቆይቷል። በመሆኑም የወንዞችን የፍሰት መጠን በዘመናዊ መንገድ የሚለካ ሥርዓት ‹ቴሌ ሜትሪ› ወደ ሥራ ይገባል።

‹ቴሌ ሜትሪ› የተባለው ቴክኖሎጂ በማንኛውም ቦታና ጊዜ ውስጥ በበይነ መረብ አማካኝነት ወቅታዊውን የወንዞች የፍሰት መጠን የሚያሳይ ነው።

ይህ ዘመናዊ የወንዞች ፍሰት መለኪያ ወቅታዊ የወንዞች የፍሰት መጠን በተንቀሳቃሽ ስልክ እና በሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ለማየት እንደሚያስችል እና በተለያዩ ወንዞች ተፋሰስ ዙሪያ ያሉ ዜጎችን ቅድመ ማስጠንቀቂያ ለመስጠትና ከአደጋ ለመከላከል እንደሚጠቅም ያነሱት ሚኒስትሩ፣ ለድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ሲሆን ደግሞ ተጨማሪ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አስረድተዋል።

የዓባይ ግድብ እንዳይገነባ የሚከላከሉ አገራት እንደ አንድ መከራከሪያ የሚያነሱት የወንዙ የፍሰት መጠን ይቀንሳል የሚል እንደሆነ ጠቁመው፤ ቴክኖሎጂው ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ ወንዙ መሃል አገር ላይ እና ድንበር ላይ ያለው የፍሰት መጠን ልኬት በቀላሉ ስለሚታይ መሰል መከራከሪያዎች እንዳይነሱ ያደርጋል ብለዋል።

በተጨማሪም የወንዞችን የፍሰት መጠን በዘመናዊ መልክ መያዝና ማወቅ የውሃ ሀብቶችን ለልማት ለማዋል ትልቅ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ጠቅሰዋል። በተመሳሳይ የንፁሕ መጠጥ ውሃ ተቋማት መረጃም ወደ አንድ ቋት እንደሚገባ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ የንፁሕ መጠጥ ውሃ ተቋማት የተደራጀ መረጃ አለመኖሩ አዳዲስ የመጠጥ ውሃ ተቋማት ግንባታን ለማከናወንም ሆነ ነባሮችን ለይቶ አስፈላጊውን ጥገና ለማድረግና ለሌሎች ጉዳዮች ችግር ሲፈጥር መቆየቱን ጠቁመዋል።

በመሆኑም በ2015 በጀት ዓመት የንፁሕ መጠጥ ውሃ ተቋማትን መረጃዎች ወደ አንድ ቋት ማምጣት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል ሲሉ ገልፀዋል።

በአሁኑ ወቅት የውሃ ሀብት መረጃዎች ባረጀ አኳኋን የተቀመጡና በአንድ ማዕከል የማይገኙ በመሆናቸው መቀየር እንዳለባቸው እና የውሃ ሀብት አስተዳደርን ለማሻሻል የውሃ ሀብቶች ከቀበሌ ጀምሮ በዘመናዊ መልኩ ተደራጅተው በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲሰነዱ ዲጂታላይዝም እንዲሆኑ ይደረጋል ብለዋል።

# ኢትዮጵያ በመንግሥታቱ ድርጅት 77ኛው ጠቅላላ ጉባዔ ወሳኝ አቋሞቿን አስረድታለች

**ጌትነት ምህረቴ**



አምባሳደር መለስ ዓለም

አዲስ አበባ፡- የመንግሥታቱ ድርጅት 77ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ኢትዮጵያ በዓባይ ግድብ እና በሰሜኑ ጦርነት ጉዳይ ወሳኝ አቋሞቿን ለዓለም ሕዝብ በግልጽ ያስረዳችበት እንደነበር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ በጉባኤው ኢትዮጵያ ወሳኝ ያለቻቸውን አቋሞች ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ አስረድታለች።

በተለይም ከዓባይ ግድብ እና ሰሜን ኢትዮጵያ ካለው ጦርነት ጋር ተያይዞ አቋሟን አስረድታለች ነው ያሉት።

በዚህም በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን በኩል የሰሜኑን ጦርነት በሰላም ለመፍታት እንዲሁም የዓባይ ግድብን በተመለከተ የጋራ ተጠቃሚነት ጋር በተገናኘ ተጠቃሚነቱም መፍትሔውም አፍሪካዊ ስለመሆኑ ያስረዳችበት መሆኑን ገልፀዋል።

ጉባኤው ዓለም ላይ ያለን ችግር ለመፍታት ከተናጠል አካሄድ ይልቅ የጋራ ጉዞ እንደሚያስፈልግ ያስገነዘበችበት እንደነበርም ጠቁመዋል።

ከጉባኤው ጎን ለጎንም የአገራት መሪዎች ጋር ግንኙነት በማድረግ የሁለትዮሽ ውይይቶች እንደነበሩ ጠቅሰው፣ 20 የሚሆኑ ውይይቶች መደረጋቸውን አንስተዋል።

በተጨማሪም ኢትዮጵያ ግንባር ቀዳሚ የሆነችባቸው በአረንጓዴ አሻራ እና በሰቆጣ ቃል ኪዳን ውስጥ የተካተቱ ሥራዎችን አጀንዳ ማድረግ ያስቻሉ መድረኮች እንደነበሩ የገለጹት አቶ መለስ፤ በተለይም ኢትዮጵያ ልምዷን ያካፈለችበት ስለመሆኑም አመላክተዋል።

ከዚህ ባለፈም ቻይና፣ ሕንድ፣ ሩሲያ፣ ኤርትራ እና ማሊን ጨምሮ ከበርካታ አገራት መሪዎችና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ጋር በመገናኘት የአገራቱን ግንኙነት የሚያጠናክሩ ጉዳዮች ላይ መምከራቸውንም ጠቁመዋል።

ከዓለም አቀፍ ተቋማት መሪዎች ጋርም በጋራ መሥራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ማድረግ መቻሉን አቶ መለስ ተናግረዋል።

የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ ሞሃሙድ በኢትዮጵያ ጉብኝት እያደረጉ መሆኑን ያነሱት ቃል አቀባዩ፣ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጋር መወያየታቸውንም ጠቁመዋል።

በውይይታቸውም አሸባሪነትን በመዋጋት እና በንግድ ትስስር ዙሪያ አብረው ለመሥራት መስማማታቸውን ገልጸዋል።

# ኢሬቻ የገቢ ምንጭና ውበት በመሆኑ ሁሉም በኃላፊነት ሊጠብቀው ይገባል

## - አንድ ሺህ ፎሌዎች በሰላም በማስከበር ሥራ ላይ ተሰማርተዋል

**ጽጌረዳ ጫንያለው**


አቶ ከድር እንዳልካቸው

አዲስ አበባ፡- የኢሬቻ በዓል የአገር የገቢ ምንጭና ውበት በመሆኑ በሰላም እንዲጠናቀቅ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት እንዳለበት የኦሮሚያ ክልል ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ እንዲሁም የኦሮሚያ ወጣቶች ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ከድር እንዳልካቸው ገለጹ። ለሰላም ማስጠበቅ ተግባሩ እንደ ክልል አንድ ሺህ ፎሌዎች መመልመላቸውና ተልዕኮ እንደተሰጣቸው ገልጸዋል።

አቶ ከድር ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደተናገሩት፤ ኢሬቻ ለኦሮሞ ማኅበረሰብ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው በዓል ነው። የሰላም ምልክት ተደርጎም ይወሰዳል። ስለሆነም በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ማድረግ ያለበትን በሙሉ እያደረገ ዝግጅቱን አጠናቋል። እንደ ኦሮሚያ ወጣት ማህበርም ሆነ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮም ክብረበዓሉ ምንም መሰናክሎች ሳይገጥሙት በሰላም እንዲጠናቀቅ ልዩ ዝግጅት ተደርጓል። ማህበረሰቡን ከማወያየትና አቅጣጫዎችን ከመከፋፈል ባሻገር አንድ ሺህ ወጣቶች ተመልምለው በዓሉን በሰላም እንዲያጠናቅቁ ተልዕኮ ተከፋፍለዋል።

ኢሬቻ አምላክ የሚመሰገንበት፤ የሚለመንበትና እርቅና ሰላም እንዲወርድ ተማጽኖ የሚቀርብበት በዓል እንደመሆኑ መጠን በሰላም ለመጠናቀቁ ከወጣቶች በላይ ኃላፊነትን የሚወስድ ማንም አይኖርም ያሉት ኃላፊው፤ በወቅቱ የሚገቡትን እንግዶች ከመቀበል ጀምሮ በየመንገዱ ላይ ችግር እንዳይገጥማቸው ከማድረግ አንጻርም ልዩ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል።

የደከሙትን መደገፍና ሕፃናት እንዳይጎዱ ማድረግ ላይም እንደ ወጣት ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት አቶ ከድር፤ በዓሉን ለማተራመስ ተልዕኮ ተቀብለው የሚመጡ አይጠፉምና እነሱን በዓይነ ቁራኛ መከታተል ላይም ቅድመ ዝግጅት እንደተደረገ ተናግረዋል።

ችግሮች ከተፈጠሩም ቶሎ ከጸጥታ አካሉ ጋር ለመፍታት የሚያስችላቸውን መንገድ እንደፈጠሩ የሚናገሩት አቶ ከድር፤ ጠላት መልካም እሴቶችን የሚገነቡ በዓላትን ለማደፍረስ የማይሞክረው ነገር ባለመኖሩ ይህ እንዳይሆን ዝግጅት ተደርጓል ሲሉም ተናግረዋል።

እንደ አቶ ከድር ገለጻ፤ ሰላምን ከማስጠበቅ አኳያ ዝግጅቱ ከመስቀል በፊት ሲከናወን የቆየ ነው። የመስቀል በዓልም በሰላም እንዲከበር የኦሮሚያ ወጣቶች ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ከከተማ አስተዳደሩና ከጸጥታ አካሉ ጋር በመሆን ልዩ ተልዕኮ ወስደው ሲሠሩ ነበር።

የኢሬቻ በዓል በሰላም እንዲጠናቀቅ ከኦሮሚያ ክልል አልፎ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጭምር እየተሠራ እንደሆነ የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፤ በቅርበት ተናበውም በከተማ አስተዳደሩ በኩል የተመለመሉ ወጣቶች እንዳሉ አስረድተዋል። ይህ ደግሞ ጠላት ያሰበው እንዳይሳካለት ያደርገዋል ብለዋል።

የኢሬቻ በዓል ሰላም መስበኪያ፣ የተጣላ መታረቂያ እንደሆነ የሚያነሱት ኃላፊው፤ ማህበረሰቡም በሀሰት ፕሮፓጋንዳ እንዳይመራ አሳስበዋል። ገና ከመስቀል በፊት ጀምሮ የአደባባይ በዓላቱ ችግር እንደሚፈጠርባቸው ሲዘራ ነበር። ሆኖም መስቀል በሰላም አልፏል። ኢሬቻም ቢሆን በሰላም ክብሩን አስጠብቆና ማህበረሰቡን አስደስቶ ያልፋል። ለዚህ ደግሞ ሕዝቡ የሚያሳስቱ የሀሰት ፕሮፓጋንዳዎችን ላለመስማት መወሰን አለበት ብለዋል።

ጠላት የሚመጣው አገር ወዳድና የኦሮሞ ተቆርቋሪ መስሎ ነው። ነገር ግን ትክክለኛውን ነገር መለየት የሚቻለው በሁሉም ሰው ላይ መተባበር ሲኖር ነውና ሁሉንም መጠራጠር ባይቻልም ክብረ በዓሉ በሚከበርበትም ወቅት ሆነ ገና ሳይጀመር የተለየ እንቅስቃሴ ሲታይ ኅብረተሰቡ ለጸጥታ አካሉ ወይም ለተመረጡት ፎሌዎች ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል ብለዋል። የጥፋት ኃይሎችን ሀሳብ ላለማስፈጸም መጣር እንደሚገባቸውም አስረድተዋል።

በዓሉ የሁሉም በመሆኑ ሁሉም ኃላፊነት ወስዶ ችግሮች እንዳይፈጠሩ መሥራት እንደሚገባው የተናገሩት ኃላፊው፤ ችግር ለመፈጸም የሚንቀሳቀሱ አካላትም ከወዲሁ ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ አሳስበዋል።

# ድምፃዊ ማዲንጎ አፈወርቅ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ



በላይ የዋለ ከያኒ ነው ብለዋል።

ማዲንጎ ሙያው የሚጠይቀውን ባህሪ የተላበሰ ጨዋ እና ጀግና አርቲስት ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ሞያውን በመውደድና ከሁሉም ነገር በላይ አገሩን በማስቀደም በህልውና ዘመቻው ወቅት የሚጠበቅበትን የፈጸመ ጀግና አርቲስት ነው ሲሉ ገልፀውታል።

በሽኝት ሥነሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የባህል እና ስፖርት ሚኒስትሩ ቀጄላ መርዳሳ በበኩላቸው ማዲንጎ በጥበብ ሥራዎቹ ህብረ ብሔራዊ አንድነት እንዲጎለብት ያደረገ አርቲስት ነው ብለዋል። አርቲስቱ አገሩን በሙያው ሳይሰስት በማገልገል ታሪክ ሠርቶ ያለፈ ድንቅ ድምፃዊ ነበር ሲሉም መስክረዋል።

ማዲንጎ በሠራቸው ሥራዎችም ስሙ ከመቃብር በላይ ይውላል ያሉት ሚኒስትሩ፤ አርቲስቱ ለአገር ያለውን ጥልቅ ፍቅር ከማሳየቱም በላይ ለሌሎች አርአያ የሚያደርገውን አኩሪ ተግባር ፈጽሞ ያለፈ ጀግና ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በሽኝት ሥነ ሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ አገር መከላከያ ሰራዊት የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ኮሎኔል ጌትነት አዳነ በበኩላቸው፤ አርቲስት ማዲንጎ አገሩን በቅንነት ያገለገለ እና አገር ወዳድ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያን ሲወዱ ለአገሩ ክብር የሚዋደቅን ወታደር መውደድ እንደሆነ አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ በተግባር አሳይቷል ያሉት ኮሎኔል ጌትነት፤ በተለይ በህልውና ዘመቻው ወቅት የሠራውን የማነቃቃት ሥራ አድንቀዋል።

እንደ ኮሎኔል ጌትነት ገለፃ፤ አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ በወጣትነት ዕድሜው በተለያዩ ሥርዓቶች በየዘመናቸው ኢትዮጵያን ያገለገሉ ወታደሮችን የማግኘት ዕድል አግኝቷል። አርቲስቱ በቅርቡ ግንባር ድረስ ዘልቆ በሙያው አገልግሏል። ይህ ደግሞ ማዲንጎ አፈወርቅ ጉዳዩ ከመጣው እና ከሄደው ሥርዓት ጋር ሳይሆን እገሩን በሕይወት መስዋዕትነት ከሚጠብቅ ወታደር ጋር መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በቅርቡ 'ቅድሚያ ለእናት አገር ኢትዮጵያ' በሚል ከሙያ አጋሮቹ ጋር በማሰልጠኛ ምልምል ወታደሮችን፤ በግንባር ደግሞ በጀግንነት እየተዋደቀ ያለውን ሰራዊት ማነቃቃቱን፣ ማበረታታቱንና ማጀገኑን አንስተዋል።

አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ፤ አገር በጦርነት ውስጥ በነበረችበት ጊዜ እና ወራሪው ኃይል እየተስፋፋ በነበረበት ጊዜ የደመራው እንጨት ወዴት ይወድቅ ይሆን ሳይል በቆራጥነት ላመነበት ሲሠራ የነበረ ጀግና ነው ሲሉም አክለዋል።

ሁሉም ንግግር ያደረጉ የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ለአርቲስት ማዲንጎ ቤተሰቦች፣ ለወዳጅ ዘመዶቹ፣ ለሙያ አጋሮቹና አድናቂዎቹ በሙሉ መጽናናትን ተመኝተዋል።

# ስግድያ ሲፈስጉ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ



ባይችሉም እናታቸውን እያስፈራሩ ልጅቷን አምጡ እያሉ ሲያንገላቷቸው እንደነበር ገልጸዋል።

የኋላ ኋላ ቡድኑ በመከላከያ ሰራዊት ተመቶ ደሴንና አካባቢውን ለቆ ሲሄድ ወደከተማዋ ተመልሰው ንግዳቸውን እንደአዲስ መቀጠላቸውን ወይዘሮ ስንታየሁ ገልጸዋል። አሁን ላይ መሥራትና የተሻለ ገቢ ማግኘት የቻልኩት መከላከያ አካባቢዬን ሰላም ስላደረገልኝ ነው የሚሉት ባለሀብቷ፤ ሰላሜን ለሚጠብቅልኝ ሰራዊት ግንባር ድረስ ወርጄ ስንቅ ማድረስ አለብኝ በሚል የስንቅ ዝግጅት ማድረጋቸውን ተናግረዋል።

ሁለት መቶ ሺህ ብር ወጪ አድርገውና አስፈላጊውን ስንቅ ከባለሙያዎቻቸው ጋር በማዘጋጀት ወደግንባር ያመሩት ወይዘሮ ስንታየሁ ታዲያ፤ ራሴ የሠራሁትን ምግብ ለሰራዊቱ ሳላጎርስ አልመለስም በሚል በእናት እጆቻቸው በአፍ በአፋቸው ሲያጎርሱ ደረስን።

እነርሱ ሕይወታቸውን ሰጥተው የእኛን ሰላም ከጠበቁ እኔ ደግሞ ያለኝን ስንቅ አዘጋጅቼ ሞራል ብሰጣቸው ምንም አይጎድልብኝም፤ ለሰራዊቱ በቀጣይም የተለያዩ ድጋፎችን አደርጋለሁ ሲሉ ግንባር ተገኝተው ድጋፍ በማቅረባቸው መደሰታቸውን ገልጸዋል።

ሌሎች ባለሀብቶችም ሠርተው ለማትረፍ ሀብት ለማካበት የሚችሉት መከላከያ በሚያደርገው ጥረት መሆኑን ተገንዝበው ያለማንም ቀስቃሽ ለሰራዊቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

# ጀግና የሕዝብ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አስተያየቱን የሰጠው አንጋፋው ድምጻዊ መሐሙድ አሕመድ ድምፃዊ ማዲንጎ ለሕዝቡ እና ለአገሩ የሠራው ሥራ ሁሌም ስሙ ከመቃብር በላይ እንዲሆን እንደሚያደርገው ተናግሯል።

ድምፃዊው በድምፃዊ ማዲንጎ ሞት የተሰማውን ጥልቅ ኀዘን ገልፆ «ዛሬ ልጄን አጥቻለሁ፤ አይዞህ ባይ ደጋፊዬን ምን ጎደለህ ባዬን አጥቻለሁ» ብሏል።

እንደ ድምፃዊ መሐሙድ ገለፃ፤ ማዲንጎ ቀደምት የሙያ አባቶቹን የሚያስብ ለእኔም ጋሼ ምን ላምጣልህ ብሎ የሚጠይቅ የሙያ ልጄ ነበር።

ሞት ቀጠሮ የለውም ያለው ድምፃዊ መሐሙድ ሁሉም እንደ ድምፃዊ ማዲንጎ ለአገሩ እና ለሕዝብ መሥራት አለበት ያለው ድምፃዊ መሐሙድ፤ ፈጣሪ ለአገር ሰላም እና አንድነት እንዲሰጥም ተመኝቷል።

ለቀብር ሥርዓቱ ከአሜሪካን አገር የመጣው ድምፃዊ መስፍን በቀለ በበኩሉ ኀዘኑ አስደንጋጭ እንደሆነበት ገልጿል።

የድምፃዊ ታምራት ደስታ ኀዘን ሳይወጣልን ነው ማዲንጎንም ያጣነው ሲል የገለፀው ድምፃዊ መስፍን፤ ከማዲንጎ ጋር የወንድማማች ያህል ቅርርብ እንደነበራቸውና የህልፈቱን ዜና እንደሰማም ሮጦ ወደ አገሩ መምጣቱን ተናግሯል።

የማዲንጎ አፈ ወርቅ አስከሬን ሽኝት ሥርዓት ላይ የሕይወት ታሪኩን ያነበበው አርቲስት ተፈሪ አለሙ በበኩሉ፤ ድምፃዊው ላለፉት ሰባት አመታት የለፋበትን የሙዚቃ አልበም እያዘጋጀ እያለ ከዚህ ዓለም በሕይወት መለየቱን ተናግሯል።

እንደ አርቲስት ተፈሪ ንግግር፤ ድምፃዊው በሙዚቃ ሥራዎቹ በእርግጥም ወጣት ተወርዋሪ ኮከብ መሆኑን ያስመሠከረ ነው። በዩቲዩብ ላይ ከ20 ሚሊዮን በላይ ተመልካች ያለው ሙዚቃ በመሥራት ብቃቱን አስመስክሯል። አርቲስቶች ችግር ሲደርስባቸው ከልመና ይልቅ እንዲረዳዱ የሚያስችል ማህበር ማቋቋሙንም ገልጿል።

በሥርዓተ ቀብሩ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስን ጨምሮ የቤተክርስቲያኗ ቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፣ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ ደመቀ መኮንን፣ የድምጻዊው ቤተሰቦች፣ ዘመድ ወዳጆቹ፣ አድናቂዎቹና ሌሎችም ተገኝተዋል።

ማዲንጎ አፈወርቅ የአንዲት ሴት ልጅ አባት ነበር። ድምፃዊ ማዲንጎ አፈወርቅ መስከረም 17 ቀን 2015 ዓ.ም ሕይወቱ ማለፉ ይታወሳል።

# ኢትዮጵያውያን እየገጠሙን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በተለያዩ ችግሮች ለሚገኙ ወገኖች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000496459001 ድጋፍ እንዲደረግ ጥሪ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊቀ አእላፍ ቀሲስ በላይ መኮንን የኃይማኖት አባቶችን ወክለው በሰጡት መገለጫ፤ መላ ኢትዮጵያውያን በኃይማኖት፣ በብሔር፣ በዘር፣ ሳንለያይ ከዚህ ፊት በጋራ ችግሮችን ስናስወግድ እንደመጣን ሁሉ አሁንም ያሉ ችግሮችን በጋራ ማስወገድ ይገባል።

ኢትዮጵያውያን በችግር ጊዜ በአንድነት አብረው እንደሚቆሙ የታወቀ ነው። አሁንም የጦርነት ሳይሆን የወደቀውን የማንሳት እኛ ለእኛ መድረስ አለብን የሚል ኃይማኖታዊና ባህላዊ እሴታችንን በመጠቀም በጋራ ለተቸገሩት ድጋፍ ልናደርግ ይገባል ነው ያሉት።

የአሁኑ ድጋፍ በዓይነት ሳይሆን በገንዘብ ብቻ መሆኑን የገለጹት ሊቀአእላፍ ቀሲስ በላይ፤ በየደረጃው የሚገኙ የኃይማኖት አባቶች ወገን ወገኑን እንዲረዳ በየቤተ እምነቶች በጎነትን ሊሰብኩ ይገባል ብለዋል።

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ ሼህ አብዱልሀሚድ አህመድ በጦርነቱ ብዙ ቤተ እምነቶች ጭምር መጎዳታቸውን አስታውሰው፤ አያት ቅድመ አያቶቻችን ውጭ ወራሪ ኃይሎች ኢትዮጵያ አገራችን እንዳይደፍሯት በአንድነት ጠብቀው አስረክበውናል። ዛሬ ባለመግባባት በተፈጠረው በእርስ በእርስ ግጭቶች ብዙ ወገኖቻችን የሞት፣ የመፈናቀልና ሌሎች ችግሮችን አስተናግደዋል። ግጭቶች እንዲቆሙ የኃይማኖት አባቶች በመጸለይ ጭምር ጥረት እያደረጉ ነው። ከዚህ ባሻገር ወገንን ለመረዳት ምንም ዓይነት ልዩነት አያስፈልግም። የኃይማኖት አባቶች በጦርነት የተጎዱ ወገኖችን ለመደገፍ ተግባብተው እየሠሩ መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስና የጉባኤው ፕሬዚዳንት ብጹዕ ካርዲናል ብርሃነ ኢየሱስ ብዙ አካባቢዎች በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ከንብረት ውድመት እስከ ሕይወት መስዋትነት የደረሰ አስከፊ ችግር ደርሷል ብለዋል። ሁሉም ወገን በህብረት ለተጎዱ ወገኖች መድረስ አለበት ሲሉም አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አይሁዳውያን ወደ ኢትዮጵያ በመጡ ጊዜ እጁን ዘርግቶ የተቀበለ ሕዝብ ነው ያሉት ብጹእነታቸው፤ አሁን የተከሰተው ችግር ኢትዮጵያን የሚመጥን አይደለም። የተፈጠሩ ሰው ሰራሽ ችግሮች ሰላማዊ መፍትሔ እንዲያገኙ የኃይማኖት አባቶች በጸሎትና በሽምግልና የቻሉትን እየሠሩ ነው። ለወገን የሚደርሰው ወገን ስለሆነ የየቤተእምነቶቹ ተከታዮች በችግር ውስጥ ለሚገኙ ወገኖች አቅማቸው የፈቀደውን ድጋፍ ሁሉ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

በሁሉም ቤተ እምነቶች ያሉ ምዕመናን በየቤተ እምነታቸው የሚደረገው ጥሪ ተቀብለው በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ድጋፍ እንዲደርጉ ጥሪ ቀርቧል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ባለ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ጉብኝት

በቅርቡ ወደ መንበረ ሥልጣን የመጡት የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሀመድ ላለፉት ሁለት ቀናት በኢትዮጵያ ይፋዊ ጉብኝት አድርገዋል። ፕሬዚዳንቱ ለጉብኝት ቦሌ ዓለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱም በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ደማቅ አቀባበል ተደርጎላቸዋል፤ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በተለያዩ መስኮች ላይ የተወያዩ ሲሆን፣ በተለያዩ ተቋማት በመገኘትም ጉብኝት አድርገዋል።

መሪዎቹ በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል ያለውን ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር ያላቸውን ፍላጎት እና ቁርጠኝነትም አረጋግጠዋል። ሁለቱ መሪዎች በተወያዩበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ኢትዮጵያ ከአዲሱ የሶማሊያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ አስተዳደር ጋር በተለያዩ ደረጃዎች ለመሥራት ዝግጁ መሆኗን አረጋግጠዋል፤ በተለይም ለኢኮኖሚው እድገት አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፤ ጠንካራና የተረጋጋች ሶማሊያ ለኢትዮጵያ ጥንካሬ እንደምትጠቅምም አስታውቀዋል።

የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሀመድ በበኩላቸው ኢትዮጵያ የተሻለች ሶማሊያን ለማምጣት ለከፈለችው መስዋእትነት አድናቆታቸውን ገልጸዋል። ሁለቱ አገሮች የጋራ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ትብብር አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የፕሬዚዳንቱ የኢትዮጵያ ጉብኝትና መሪዎቹ በጋራ ለመሥራት ያሳዩት ፍላጎትና ቁርጠኝነት ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ፋይዳ ቢኖረውም፣ ከዚያም በእጅጉ የተሻገሩ ፋይዳዎች ይኖሩታል። ለኢትዮጵያና ለሶማሊያም አልፎ ተርፎም ለምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና የላቀ ፋይዳ አለው።

እንደሚታወቀው ሁለቱ አገሮች ረጅም ድንበር የሚጋሩና ጎረቤታሞች ናቸው። በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነታቸውም ዘመናትን አብረው የዘለቁ፣ የሚጋሩት ቋንቋና ባህል ያላቸውም ናቸው።

ሶማሊያ ለሁለት አስርት ዓመታት መንግሥት አልባ ሆና አገሪቱ በሰላም እጦት የተነሳ ቀውስ ውስጥ በወደቀችበት ወቅት አያሌ ሶማሌያውያን ኢትዮጵያን መጠለያቸው አድርገዋል፤ ሶማሊያ ሰላም በሆነችበት ዛሬም በአዲስ አበባ ጥቂት በማይባሉ መንደሮች በርካታ ሶማሌያውያን ከወንድም አህት ኢትዮጵያውያን ጋር በፍቅርና በሰላም ይኖራሉ።

ከሁለት አስርት ዓመታት በኋላ አገሪቱን ከመንግሥት አልባነት ወደ ባለመንግሥትነት በማሸጋገር በኩል የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት ሚና ከፍተኛ ቢሆንም፣ በዚህ ውስጥ ኢትዮጵያ የተጫወተችው ሚና የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል። ኋላም ላይ የአፍሪካ ሰላም አስከባሪ ኃይል(አሜሶም) በአገሪቱ ሲሰማራም የኢትዮጵያ ድርሻ ከፍተኛ እንደነበር ይታወቃል። በአገሪቱ የተመሠረተው አዲስ የሽግግር መንግሥት እንዲጸና አልሸባብና መሰሎቹን በመዋጋት በኩል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የከፈሉት መስዋዕትነትም ታሪክ ሲዘክረው የሚኖር ሀቅ ነው። ፕሬዚዳንቱም ለእዚህ መስዋዕትነት ያላቸውን አድናቆት መግለጻቸውም ይህንኑ ያመለክታል።

ኢትዮጵያ የሶማሊያን ሰላም መሆን አሁንም ትርጉሙ ብዙ እንደሆነ አጥብቃ ታምናለች። ኢትዮጵያ በሶማሊያ ችግሮች በተነሱ ጊዜም ጎረቤት ሰላም ካልሆነ አገር ሰላም አታገኝም ብላ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ዓለም ዳር ቆሞ ሲመለከት፣ አንዳንዶችም ሞክረው ሳይሳካላቸው ሲቀርና አገሪቱን ጥለው ሲሄዱም ኢትዮጵያ ግን ጉዳዩን የራሷ አድርጋ በመያዝ ለሶማሊያ ሰላም አጥብቃ ሠርታ የዛሬዋ ሶማሊያ እንድትታይ ማድረግ ችላለች።

የጎረቤት ሰላም የራስም ሰላም ነውና ይህ ሰላም ዘላቂ እንዲሆንም ትፈልጋለች። በሶማሊያ የዘራችው የሰላም ፍሬ ፍሬያማ መሆኑን አይታለች፤ የአሁኑ የሶማሊያ ፕሬዚዳንትም ሆነ ከእሳቸው ቀደም ያሉት ወደ ሥልጣን የመጡት የቀድሞው ፕሬዚዳንት በሰላማዊ መድረክ መምጣታቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በሶማሊያ የዘሩት የሰላም ዘር ውጤት ነው።

ዛሬም እንደዚያው ነው። ሁለቱ አገሮች ዓለም አቀፉ አሸባሪ አልሸባብ የተባለ የጋራ ጠላት አላቸው። የዚህን አሸባሪ ቡድን ህልውና ለማክተም የሁለቱ አገሮች ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ መሸጋገር የማይተካ ሚና አለው።

አልሸባብ የኢትዮጵያና የሶማሊያ ጠላት ብቻ አይደለም፤ የምሥራቅ አፍሪካም ክፉ ጠላት ነው። በዚህ ቡድን ሶማሊያ በእጅጉ ተጎድታለች ተፈትናለችም። የዚህ አሸባሪ ህልውናው እንዲያበቃ ለማድረግ የምሥራቅ አፍሪካን አገሮች ብቻ ሳይሆን የመላ አፍሪካም፣ የዓለምም ትብብር የግድ ይላል።

አልሸባብ ብዙዎቹ ሴራዎቹ በኢትዮጵያ ከሽፈውበታል። ኢትዮጵያ ቡድኑ በገባበት ገብታ መትታዋለች። በቅርቡም ከአገር ውስጥ ባንዳዎች ጋር ሆኖ ጥቃት ቢሰነዝርም የገባበት ገብታ ህልሙን ቅዥት አድርጋበታለች።

ኢትዮጵያ የአሸባሪውን ትህነግ ህልውና ለማሳጣት እያደረገች ባለችው ርብርብ፣ በምሥራቅ ኢትዮጵያም አልሸባብ ላይ እያካሄደች ያለችውን ዘመቻ ከዳር ለማድረስ የኢትዮጵያና የሶማሊያ መንግሥታት አብረው ለመሥራት የያዙት አቋም ወሳኝነት ይኖረዋል። አገሮቹ ይህን አቋምና ቁርጠኝነት መሬት ላይ እንዲወርድ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

የአገሮቹ ስምምነት ለኢትዮጵያም ለሶማሊያም በአጠቃላይም ለምሥራቅ አፍሪካ ለመላው አፍሪካ ሰላም ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚም ይጠቅማል፤ ኢትዮጵያ የወጪ ምርቶቿ መዳረሻ ከሆኑት አገሮች መካከል እ.አ.አ በ2021 ሶማሊያ በመሪነት ትገኛለች። ይህ ሁኔታ በወጪ ንግድ ከፍተኛ መነቃቃት እያሳየች ላለችው ኢትዮጵያ ሶማሊያ ትልቅ ገበያ እንደምትሆን ያመለክታል። ሶማሊያ በወጪ ንግዱ ብቻ ሳይሆን በወደቦቿም ለኢትዮጵያ ጥሩ አማራጭ መውጫዎች በመሆን ታገለግላለች።

እንደምሥራቅ አፍሪካም እንደ አፍሪካም በተያዙት ቀጣናዊ የኢኮኖሚ ትስስሮች ሶማሊያና ኢትዮጵያ ግንኙነታቸውን በሁሉም መስክ ማጠናከር የሚችሉባቸው መስኮች ያሏቸው እንደመሆናቸው የፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሀመድ የኢትዮጵያ ጉብኝት ፋይዳው ከፍተኛ ነው!

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ያልተገመቱ ተጽዕኖዎች እያስከተለ ያለው የዲጂታል ዘመን ፕሮፓጋንዳ

**መሳኩ ኤርሴ**

ቀደም ባሉ ዘመናት የፕሮፓጋንዳ መልእክቶችን ለማስተላለፍ የዜና ዘገባዎች፣ የመንግስት ሪፖርቶች፣ መጽሐፍት፣ በራሪ ጽሑፎች፣ ፊልሞች፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን እና ፖስተሮች ጥቅም ላይ ሲውሉ ነበር። ዛሬ ግን የፕሮፓጋንዳ ስራዎች እላይ በተጠቀሱት የፕሮፓጋንዳ መልዕክት ማስተላለፊያ መሳሪያዎች ብቻ የታጠረ አይደለም። የዲጂታል ዘመን ፕሮፓጋንዳ ሳቢ በሆነ አዲስ የጥበብ አገላለጽ የሚገለጽበት ዘመን አምጥቷል። እሱም ሜም ይባላል።

ሜም የሚለው ቃል ከግሪክ ''ሚሜማ'' ከሚል ቃል የመጣ ሲሆን፤ ትርጉሙ “የተመሰለ” ማለት ነው:: ሜም ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቀው በ1976 በብሪቲሽ የዝግመተ ለውጥ ባዮሎጂስት ሪቻርድ ዳውኪንስ ነው። ባዮሎጂስቱ ሜምን ያስተዋወቀው ''ዘ ሰልፊሽ ጂን'' በተባለው ስራው ውስጥ ነው:: ሜሞች በውጭ ሀገራት ከተለመደ የቆየ ቢሆንም በሀገራችን የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው::

ሜሞች መጀመሪያ ላይ ሰዎችን ለማሳቅ እና ለማዝናናት ዓላማ ጥቅም ላይ ሲውሉ የነበረ ቢሆንም፤ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የፖለቲካ ዓላማ ያነገቡ ሜሞች የበይነመረብ ምህዳር መቆጣጠር ጀምረዋል። ከዲጂታል ዘመን ቀደም ብለው ይሰሩ እንደነበሩት የፕሮፓጋንዳ ፖስተሮች፤ ፖለቲካዊ ዓላማ ያነገቡ ሜሞች አስደናቂ እይታዎችን ከውጤታማ ተግባቦት ጋር በማጣመር የተመልካቹን አስተሳሰብ ወይም ንቃተ ህሊና የመለወጥ ዓላማ አንግበው እየተሰሩ ነው። ፖለቲካዊ ዓላማ ያነገቡ አብዛኛዎቹ ሜሞች ተቃዋሚዎችን ሰብአዊነት ለማሳጣት እና ፖለቲከኞች ያነገቧቸውን የፖለቲካ ዓላማ ግላዊ አድርገው በማቅረብ ተቀባይነት እንዳይኖረው ማድረግን ዓላማ አድርገው እየተሰራ ይገኛል።

ከዲጂታል ዘመን በፊት የተለያዩ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያዎችን በመጠቀም ፕሮፓጋንዳ በሚሰራበት ወቅት ትልቅ ሚና ይጫወቱ የነበሩት አብዛኛዎቹ መርሆዎች ግን ዛሬም እንደ መጠቀሚያ ዘዴዎች ለዲጂታል ዘመን በሚመጥን መልኩ ተሻሽለው ቀጥለዋል። ቀደም ባሉት ዘመናት በፕሮፓጋንዳ ውስጥ የነበሩ መርሆዎችን እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ፕሮፓጋንዳ በረቀቀ መንገድ እየተሰራ ነው። ስሜት መኮርኮር፣ “እኛ” ከ “ጠላት” ጋር በሚል በጎራ መከፋፈል፣ ቡድኖችን እንዲሁም ግለሰቦችን በስፋት መድረስ እና ፕሮፓጋንዳ መሆኑ እንዳይታወቅ በተቻለ መጠን ድብቅ ማድረግ የሚሉ መርሆዎች ዛሬም ጥቅም ላይ ይውላሉ።

ህዝቦች የሚያቀራርብ እና ፍቅርን የሚሰብኩ ሜሞች ቢለመዱ የሚበረታታ ነበር። አብዛኛውን ጊዜ ሜሞች የህዝብን ጥቅም ለማራመድ የተነደፉ እና የተቀነባበሩ የማይሆኑበት አጋጣሚ አለ። በአንጻሩ አፍራሽ ዓላማ ያነገቡ በርካታ ሜሞች ማህበራዊ ሚዲያው ላይ በስፋት እየታየ ነው።

ጽንፍ የረገጡ እና ሌሎችን አስተሳሰቦችን የመጨፍለቅ ዓላማ ያነገቡ አካላት ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም የተሳሳተ መረጃን ለማሰራጨት የሜም ፎርማትን እንደ መሳሪያ እየተጠቀሙ መሆኑ ጉዳዩን አሳሳቢ ያደርገዋል። ሜሞችን ለዘረኛ እንቅስቃሴዎች የሚጠቀሙ ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሆኑን ለመረዳት ማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚዘዋወሩ ሜሞችን መመልከት ብቻ በቂ ነው።

ሀይማኖቶችን እና ብሄሮችን የሚያጠለሹ ሜሞችን መመልከት እየተለመደ ከመጣ ሰነባብቷል። ሌሎች አካላት ላይ ጥላቻ ከመስበክ ባሻገር ለዘረኛ ንቅናቄያቸው ድጋፍ ለማሰባሰብም እየተጠቀሙበት ነው። የሀገር መሪዎችን እና የህዝብ አገልጋይ ተሿሚዎችን መልካም ስብዕና ለማጠልሸት ብሎም በህዝብ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት ለማሳጣት በትኩረት ይሰራል።

በጣም የሚያስፈረው ደግሞ አዲሱ የፖለቲካ ጥበብ የሜም ፎርማት ከዲጂታል ዘመን በፊት ከነበሩት የፕሮፓጋንዳ ፖስተሮች እጅግ የላቀ የመሰራጨት አቅም ያለው መሆኑ ነው። ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም በፍጥነት እንዲሰራጭ እየተደረገ ነው። ከዲጂታል ዘመን በፊት ፕሮፓጋንዳዎች በዋናነት በመንግስት ነበር የሚሰራው።

ዛሬ ግን በመንግስት በተለያዩ መንገዶች ከሚሰሩ ፕሮፓጋንዳዎች ይልቅ፣ ማንኛውም ሰው፣ የሀገር ውስጥም ይሁን አለማቀፋዊ፣ የፖለቲካ አጀንዳ ያላቸው ቡድኖች እና ግለሰቦች ፖለቲካዊ ዓላማ ያነገቡ ምልክቶችን፣ ምስሎችን እና ዲጂታል ጥበብን ተጠቅመው የፖለቲካ ዓላማን ለማራመድ ብዙ ተመልካቾች ጋር ማድረስ እየቻሉ ነው።

የፕሮፓጋንዳ ፖስተሮች ስለ ፖለቲካ ነክ ስነ-ጥበባት በስነ-ልቦና ላይ ስለሚያሳድሩት ተፅእኖዎች ብዙ ያስተምሩናል። ሜሞች የኢንተርኔት ባሕል የፈጠረው የሞኝ የተዝረከረከ ጨዋታ ቢመስሉም በማስታወቂያ ላይ የተደረጉ ጥናቶች እና መረጃዎችን ወስደን በምናይበት ጊዜ ሜሞች የሰዎችን ንቃተ ህሊና ሊለውጡ እንደሚችሉ ያሳያሉ። አንዳንድ የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት ሰዎች ከፕሮፓጋንዳ ነፃ አይደሉም። አንዴ የተሰራ ፕሮፓጋንዳ የሰዎች ህሊና ላይ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ተፅዕኖ የማሳደር አቅም አላቸው። ከብዙ ዓመታት በፊት የተሰሩ የፕሮፓጋንዳ ስራዎች በሰዎች ጭንቅላት ውስጥ አይጠፉም።

በይነመረብ የፈጠረውን እድል በመጠቀም አፍራሽ ዓላማ ያነገቡ ሜሞችን በተመሳሳይ ሰዓት ማንኛውም ሰው በጅምላ ሊያባዛው ይችላል። በደቂቃዎች ውስጥ ሚሊየኖች ጋር የመድረስ እድል አላቸው። በሜሞች አማካኝነት ከሚተላለፉ መልዕክቶች ውስጥ እውነተኛውን እና ልቦለድ ለመለየት ከባድ ነው። በተለይም ተራው ማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ በሜሞች አማካኝነት የሚተላለፉ መልዕክቶችን ሳያስበው የመቀበል እድሉ ከፍ ያለ ነው።

በአሁኑ ወቅት የበይነ መረብ ምህዳሩ ላይ እየተለመዱ ያሉት የፖለቲካ ዓላማ ያነገቡ ሜሞች የፖለቲካ ታሪካችን ቋሚ አካል ሆነው ይቀጥላሉ ወይስ አይቀጥሉም የሚለውን ጊዜ የሚመልስ ይሆናል። ለጊዜው ግን የሜሞችን ያልተገመቱ ተጽዕኖዎች በግልጽ እያየን ነው። በመሆኑም መፍትሄ ሊፈለግለት ይገባል። በተለይም ሀይማኖት ነክ እና ብሄር ነክ ሜሞች ላይ ቁጥጥር የሚደረግበት መንገድ ሊበጅ ይገባል።

## ነፃ ሃሳብ

# በምግብ እራስን ለመቻል የኩሬ ልማት ዘመቻ ሚና

ጋሹ ሃብቴ (ዶ/ር)

**ጋሹ ሃብቴ (ዶ/ር) ከጂማ እርሻ ኮሌጅ ዲፕሎማ፣ከዓለማያ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪ፣ከኦክለሆማ እስቴት ዩኒቨርስቲ ደግሞ የዶክትሬት ዲግሪ በእርሻ ምጣኔ አግኝተዋል ።በግብርና ሚኒስቴር በእርሻ ወኪልነት፣ በጂማ እርሻ ኮሌጅ በአስተማሪነት፣በክፍል ኃላፊነት፣በተማሪዎች ዲንነትና በኮሌጅ ዲንነት አገልግለዋል ። በአሜሪካን ሀገር ደግሞ በአርከንሳስ እስቴት ዩኒቨርስቲ በአስተማሪነት ሠርተዋል።**

ኢትዮጵያ በአፍሪካ የውሃ ማማ ተብላ የሚነገርላትና የምትታወቅ ሃገር ብትሆንም ሀብቱን ተጠቅማ ሕዝቦቿን መመገብ በሚያስችል ቁመና ላይ መገኘት አልቻለችም። ከዚህም የተነሳ ዛሬም ቢሆን ይህንን ሀብት በአግባቡ ተጠቅሞ በምግብ እህል እራስን የመቻል ጉዳይ ትልቅ ሀገራዊ አጀንዳ እንደሆነ ነው ፡፡ ይህንን ሀገራዊ አጀንዳ ወደ ተጨባጭ ልማት ለመለወጥ ሰፊ የሆነ ኩሬ ውሃ የማልማት /የመጠቀም/ ዘመቻ ማድረግ ያለብን ይመስለኛል።

ኩሬ ማለት ውሃን ከተፈጥሯዊ ፍሰት አቅጣጫውን አስለውጦ ለሰዎች ጥቅም በሚውል መልኩ ማጠራቀም ማለት ነው፡፡ የወንዞችን ፍሰት አቅጣጫ በመግታት፣ በመለወጥና ማጠራቀሚያ በማዘጋጀት ኩሬ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የጎርፍ ውሃን በተዘጋጀ ቦታ በማጠራቀምና ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆይ በማድረግ ለሰዎች ጥቅም ማዋል በሚቻል መልኩ ኩሬ ሊፈጠር ይችላል፡፡

ጉድጓድ ተቆፍሮ የሚገኝ ውሃም የኩሬ ውሃ ሊሆን ይችላል፡፡ እጅግ በጣም ትንሽ ኩሬ ደግሞ ሰዎች በጓሯቸው በተለያየ መንገድ የሚያጠራቅሙት ውሃ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ የኩሬ ውሃ ማለት ሰዎች አስፈላጊ ሲሆን የሚጠቀሙበት የመጠባበቂያ ውሃ ማለት ነው። የኩሬ ውሃ እኔ ካልኩት በተለየ ሌሎች በሌላ መልኩ ሊገልጹት ይችላሉ። በአጠቃላይ ግን የኩሬ ውሃ ማለት ለተለያየ ተግባር የሚውል ለመጠባበቂያ የተጠራቀመ ውሃ ነው። በተለይ ዝናብ በሌለበት ወቅት በአጭር ጊዜ ለሚደርሱ ለማንኛቸውም ምርት ማምረቻ የሚውል ውሃ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ገና ከመጀመሪያው ኩሬ ማለት ግድብ ማለት እንዳልሆነ ለማሳሰብ እፈልጋለሁ።

ዘመቻውስ ከየት መጣ ለምንስ አስፈለገ ለምትሉት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመደበኛነት ከሚሠራቸው በርካታ ሥራዎች በተጨማሪ በዘመቻ በርካታ ሥራዎችን ለረጅም ጊዜ ሲያከናውን የቆየ ሕዝብ መሆኑ ይታወቃል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በቢዝማርክ ጀርመን አሜሪካንን ጨምሮ ስምንት ሀገሮች አፍሪካን ለመከፋፈል ያደረጉትን ስምምነት በዘመቻ እራሱን በመከላከል ወረራውን ያመከነ ብቸኛ ሕዝብ ነው። በምስራቅና በሰሜን በተደጋጋሚ የገጠሙትን ጦርነቶች በአሸናፊነት የተወጣናቸውም ሕዝብ ባደረገው በርካታ የዘመቻ ትብብር ነው።

ሀገርን ከመከላከል በተጨማሪ በርካታ የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዘመቻዎችን በጋራ ሲያከናውን ዘመናትን ያሳለፈ ሕዝብ ነው። ስለዚህ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መጠኑ ይነስና ይለያይ እንጂ በዘመቻ መሥራት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየ ልማዱ ነው። በመሆኑም ሀገራዊ የኩሬ ምስረታ ጥሪና ዘመቻ ቢደረግ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የኩሬ ምሥረታ ሥራ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሊሠራ ይችላል።

ከዚህም በተጨማሪ አሸዋማና ውሃን መያዝ ለማይችል መሬት አካባቢ፣ በዘመቻ የሃገር ጥሪ ነውና የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ መሰሎችንና ተመሳሳይ ምርቶችን ማምረት ለሚችሉ ባለፋብሪካዎችና ተባባሪዎች ሁሉ መንግሥት የትብብር ጥሪ ቢያደርግ፣ ቢያቀነባብርና አስፈላጊውን ድጋፍ ቢያደርግ ውሃ ለመቋጠር ችግር ያለበት አካባቢ በአብዛኛው በዝናብ ጊዜ ከሚገኝ ውሃ አነስተኛ ኩሬ በመሥራት ተጠቃሚና ባለቤት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለኝ።

ኢትዮጵያ በዓለም በሕዝብ ቁጥር 12ኛ ስትሆን በመሬት ስፋት ደግሞ 27ኛ ነች። የሕዝቧ ብዛትም በፍጥነት እያደገ ያለችም ሃገር ናት፡፡ ስለዚህ ሕዝቧን ለመመገብ በዝናብ ብቻ የሚመረተው ምርት (ከ95% በላይ) በቂ ስለማይሆን ገበሬው በመስኖ የማምረት ጥረትን በመጨመር አጠቃላይ ምርቱንም ማሳደግ አለበት፡፡በመጪዎቹ 25 እና 50 ዓመታት ሕዝቧ በጣም ስለሚያድግ ለረጅም ጊዜ ስንከተል የቆየነውን አሠራርና አመራረት መቀየርና ማሻሻል አለብን።

**ኢትዮጵያ በዓለም በሕዝብ ቁጥር 12ኛ ስትሆን በመሬት ስፋት ደግሞ 27ኛ ነች። የሕዝቧ ብዛትም በፍጥነት እያደገ ያለችም ሃገር ናት፡፡ ስለዚህ ሕዝቧን ለመመገብ በዝናብ ብቻ የሚመረተው ምርት (ከ95% በላይ) በቂ ስለማይሆን ገበሬው በመስኖ የማምረት ጥረትን በመጨመር አጠቃላይ ምርቱንም ማሳደግ አለበት፡፡በመጪዎቹ 25 እና 50 ዓመታት ሕዝቧ በጣም ስለሚያድግ ለረጅም ጊዜ ስንከተል የቆየነውን አሠራርና አመራረት መቀየርና ማሻሻል አለብን።**

ስለሆነም በመስኖና በተጠራቀመ ውሃ የእራሳችንን ምርት ማምረትና የመደጎም ልምዱን በተፋጠነ ሁኔታ በገጠር ብቻ ሳይሆን በከተማም ጭምር ማሳደግ አለብን። የዚህን አይነት ልምድ ያላቸው አካባቢዎች በኢትዮጵያ ስለአሉን የእነሱን ተሞክሮ ሃገራዊ ለማድረግ ጥረት ማድረግም ያለብን ይመስለኛል፡፡

በዓለም ካሉ ሃገሮች ጋር ሲነጻጸር ኢትዮጵያ ባላት የእርሻ ወኪሎች ቁጥር ቻይና ካላት 910,000 የእርሻ ወኪሎች በመቀጠል በ108,576 የእርሻ ሠራተኞች ቁጥር ሁለተኛ ነች ( GFRAS: Global Forum for Rural Advisory Services)። በሦስተኛነት ደግሞ 1.3 ቢሊዮን ሕዝብ ያላት ሕንድ ናት፣ 90,000 የእርሻ ወኪሎች አላት። ስለዚህ በኢትዮጵያ የግብርናውን ዘርፍ ለማገዝ የተሠማራ በርካታ ሙያተኛ አለ ማለት ነው። ከወረዳ አስተዳዳሪዎችና ሌሎች ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር የኩሬ ዘመቻ ቢደረግና እያንዳንዱ የግብርና ሠራተኛ ከአምስት እስከ ሰባት ኩሬዎችን ቢያስተባብር ከአምስት መቶ ሺህ እስከ ሰባት መቶ ሺህ (500,000 እስከ 700,000) ኩሬዎችንና የተገደበ የውሃ ምንጮችን ወይም ከምችቶችን በዓመት ልንሠራ ወይም ልንፈጥር እንችላለን ማለት ነው።

ይህ ሊሆን አይችልም የሚል ካለ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የእርሻ ወኪሎችና ገብሬው ከተባበሩ ምን ሊሠሩ እንደሚችሉ ልምድና ግንዛቤ የሌለው ሰው ብቻ ነው። ምክንያቱም በበጋው ወራት የእርሻ ሠራተኞች በቂ ጊዜ አላቸውና ነው። ፍላጎት፣መሠረታዊ እቃዎች፣ተጨማሪ በጀት፣የማስተባበር፣ የማነሳሳት፣ኃላፊነትን መቀበልና ከሥራ መደብ ጋር የተቆራኘ የዘመቻ ግዴታ ስለመኖሩ እርግጠኛ መሆንና ክትትል በማድረግ ይህን ግብ ለሟሟላት ምንም አዳጋች ሊሆን አይችልም ብል በፍጹም ማጋነን አይሆንም።

ከላይ ለጠቀስኩት የይቻላል ድምዳሜ ያደረሰኝ በልጅነቴ የማውቃቸው የተለያዩ የአራት ሰዎች ሥራና እኔም በእርሻ ወኪልነት ሠርቼ ስለነበረ ነው። አባ ወልደየስ ፊደል ያስቆጠሩኝ መምህሬ ሲሆኑ ትንሽ 2 ሜትር ጥልቀት በ3 ሜትር ስፋት ገደማ ካለው በጓሮአቸው ከሚገኝ ኩሬ በበጋ ወራት በምንም መልኩ ጎመንና ሌላ አትክልት አይጠፋም ነበር። ወይዘሮ ሎሚ የሚባሉ የጉራጌ አገር ሴት ደግሞ በጓሮአቸው በነበራቸው በሁለት ሰባራ ጋን ከሚጠራቀም ውሃ በበጋ ወራት በምንም መልኩ ጎመንና ቃሪያ እሳቸውም አያጡም ነበር።

ሌላው አቶ ሽበላው ሲሆን እሱ ደግሞ ሁል ጊዜ ውሃ ከወንዝ በመሸከምና በማጠራቀም በበጋው ወራት ከራሱ ተርፎት በገንዘብ የሚሸጠውን ጎመን ያመርት እንደነበር አውቃለሁ። ሌላው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤታችን ዳይሬክተር በነበሩት በአቶ ታደሰ ኃይለመስቀል አስተባባሪነት የተዘረጋውና በተማሪዎችና በአካባቢ ገበሬዎች የተቆፈረው ከአምስት ኪሎ ሜትር በላይ እርዝመት የነበረው የቦይ ውሃ ነው። ይህ ቦይ ለአካባቢው ገበሬዎች የጓሮ አትክልት ለማምረትና ለከብቶች የውሃ መጠጫነት በጣም ይጠቅም እንደነበረና በትምህርት ቤታችንም በርካታ የአትክልት አይነቶችን እናመርትበት እንደነበረ ስለማውቅና ስለማስታውስ ነው። ከነዚህ ሁሉ ልምዶቼ በተጨማሪ በግብርና ሚኒስቴር በእርሻ ወኪልነት ለአጭር ጊዜም ቢሆን የአገለገልኩ ስለነበረም ነው ይቻላል የምለው።

ኩሬዎች በየወንዙ የሚፈሰውን ውሃ በከፊል በማቆምና የጎርፍ ውሃን በማጠራቀም የሚፈጠሩ ሲሆን ትነትን በመጨመር የጠፉ ደኖችንን በመተካት ለዝናብ መኖር ሊረዱ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ እድገት የመሬት ጥበትን ፈጥራል። ጥበቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው የሚሄደው። ስለዚህ ወንዞችንና ለእርሻ የማይውሉ ሸለቆዎችን ለውሃ መቋጠሪያ ብንጠቀም በርካታ ኩሬዎች በየአካባቢው ሊኖሩ ይችላሉ። ከነዚሁ በርካታ ኩሬዎች የሚተነው ውሃም እርጥበት በመፍጠር ዝናብ ለማግኘት የራሱ ሚና ሊኖረው ይችላል።

ከደን ተከላው ጎን ለእርሻ የማይውሉ ቦታዎች ላይ ውሃ ቢተኛ ከፍተኛ የሆነ ትነት ማግኘት የሚቻል ይመስለኛል። የኩሬዎች በየአካባቢው መኖር ከእርሻ ምርትና ዝናብ ለማግኘት ከመጥቀም ሌላ ለዓሳ ምርት ማምረቻና ለተጨማሪ ምግብ ምንጭ ሊያገለግሉ ይችላል። ከነዚህም በላይና በተጨማሪ የበርካታ ኩሬዎች መኖር የሃገራችን ጸጋ የሆነውን የከብት እርባታን በመኖ ምርት በመደገፍ ከእንስሳት የሚገኝ ተዋጽዖን ለማሳደግ በከፍተኛ ደረጃ ሊረዳ ይችላል።

በአጠቃላይ በኩሬ የተከማቸ ውሃን የመጠቀም ልምድ የእርሻ ሰብል ምርትን ይጨምራል፣የምግብ እጥረትን ይቀንሳል፣በድርቅ ጊዜ ያለውን የምግብ ምርት ማነስ ይደጉማል፣ ለከብት መኖ ምርት ማደግ ይረዳል፣ ለአካባቢ የአየር ሁኔታም ይጠቅማል። በመሆኑም የኩሬ ዘመቻ በመጀመሪያ የሚረዳው በምግብ እራስን መደጎምን ይሆንና ከጊዜ በኋላ ደግሞ በምግብ እራስን የመቻል አቅምን ሊያጎናጽፈን ይችላል። ሰለሆነም የኩሬ ዘመቻን እውን ለማድረግ መንግሥት ፕላን አውጥቶ፣ ዘርዘር ያለ ፕሮግራም ሠርቶ፣በጀትም መድቦለት፣ የተቀናጀ የሥራ አፈጻጸምና የግምገማ ሥርዓት አውጥቶ ክትትል የተሞላበት ጥረትና ድጋፍ ያለው ሥራ ቢሠራ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ምንም አያጠራጥርም።

ከዚህም በተጨማሪ በግልም ሆነ በጋራ ለሚሠሩ ኩሬዎች ሁሉ የየአካባቢው የእርሻ ወኪሎችና የወረዳው የአስተዳደር ሠራተኞች ከፍተኛ ጥረትና የማስተባበር ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ጥረት ለተከታታይ ዓመታት ከተከናወነ በኢትዮጵያ የእርሻ ምርትን ማሳደግና በምግብ እራስን መቻልን ብዙም አስቸጋሪና አጠራጣሪ አይሆንም ማለት የሚቻል ይመስለኛል።

{ጋሹ ሃብቴ (ዶ/ር) ከጂማ እርሻ ኮሌጅ ዲፕሎማ፣ከዓለማያ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪ፣ከኦክለሆማ እስቴት ዩኒቨርስቲ ደግሞ የዶክትሬት ዲግሪ በእርሻ ምጣኔ ሲኖረኝ በግብርና ሚኒስቴር በእርሻ ወኪልነት፣ በጂማ እርሻ ኮሌጅ በአስተማሪነት፣በክፍል ኃላፊነት፣በተማሪዎች ዲንነትና በኮሌጅ ዲንነት አገልግያለሁ። በአሜሪካን ሀገር ደግሞ በአርከንሳስ እስቴት ዩኒቨርሲቲ በአስተማሪነት ሰርቻለሁ፤}

# ኢሬቻ

ግርማ መንግሥቴ

የኢሬቻ በዓል በነገው እለት ይከበራል። በመሆኑም ከወዲሁ፤

ኢሬቻ የአንድነትና የአብሮነት ዓርማ ነው!

ኢሬቻ ለሰላም፤ ኢሬቻ ለፍቅር!

Irreechi nageenyaaf Irreechi jaalalaaf

Irreechi Falaasama Dhugeeffannaa Oromooti!

የሚሉ ድምፆች ከፍ ብለው በመሰማት ላይ ናቸው።

በነገው እለት የሚከበረውን የኢሬቻ በአል አስመልክቶ በርካታ ዝግጅቶች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

በአዲስ አበባ "ኢሬቻ ለሰላም፤ ኢሬቻ ለፍቅር"፤"ኢሬቻ የሰላምና የወንድማማችነት/የእህትማማችነት ተምሳሌት "ኢሬቻ የፍቅርና የወንድማማችነት መገለጫ ነው! ኢሬቻ የምስጋናና የእርቅ ተምሳሌት ነው!" በሚሉ መሪ ቃላት የተለያዩ ዝግጅቶች በመከናወን ላይ ነው።በኃይማኖት አባቶችና አባ ገዳዎች ምርቃት (ኤባ) የተጀመሩ የፓናል ውይይቶች ሲካሄዱ ሰንብተዋል። በተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ ውይይቶች ተደርገዋል። በየፓናሎቹ (ሕዝባዊ ውይይቶቹ)ም ከከተማ አስተዳደሮቹ አመራሮች ጀምሮ በተዋረድ እስከታች የሚገኙት አመራሮች፣ አባ ገዳዎች፣ ሃደ ሲንቄ፣ ቄሮ፣ ቀሬ እና የአካባቢው ነዋሪዎችም መገኘታቸው ታውቋል።

ሕዝባዊ ውይይቶች ከተካሄደባቸው ክፍለ ከተሞች አንዱ በሆነው፣ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 አስተዳደር የተካሄደውና ከአለባበስ ጀምሮ ሕብረ-ብሔራዊነት የታየበት መሆኑ የተነገረለት የፓናል ውይይት "ኦሮሞ" ማለት በአጭሩ ውሃ ጠይቀህ ማርና ወተት የሚሰጥ፣ እናትና አባት የሌላቸውን ተቀብሎ በጉዲፈቻ መልክ ለወግ ማዕረግ የሚያበቃ፣ የቅንነት፣ የመቻቻል እና የአብሮነት ዕሴት በእጅጉ የሚታይበት፤ የሀገር ካስማ (ዋልታና ማገር) ነው።" የሚለው ሀሳብ ጎልቶ የወጣበት ፓናል መሆኑን እዚህ ላይ በማሳያነት ጠቅሶ ማለፍ ተገቢ ነው።

ባለፈው ዓመት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴክተር ተቋማት ማስተባበሪያ ያዘጋጀው የ2014 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል አከባበር በተመለከተ ከ700 (የተወሰኑት እንኳን ለትውልድ ይተላለፉ ዘንድ በመጽሐፍ መልክ ቢዘጋጁ መልካም ነበር) በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተገኙበት ውይይት ተካሂዶ የነበረ መሆኑ፤ በውይይቱ የኦሮሞ ተወላጆች ብቻ ሳይሆኑ ከሁሉም ብሔር የተውጣጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊ የነበሩ መሆናቸውን በወቅቱ ተነግሮናል። የዘንድሮዎችን በቁጥር ባናውቅም በጥናትና ምርምር ሥራዎች የተደገፉ ፓናሎች መካሄዳቸውን አውቀናል።

እነዛ ሰነዶች እንደተስማሙበትም ሆነ የዘንድሮውን የኢሬቻ በዓል አስመልክተው እየወጡ ካሉ መረጃዎች፣ እየተላለፉ ካሉ መልዕክቶችና እየተሰጡ ካሉ መግለጫዎች መረዳት እንደሚቻለው፤ "ኢሬቻ" እና "የኢሬቻ በዓል"፤ እንዲሁም "የኢሬቻ በዓል አከባበር ሥነሥርዓት" የሚከተለውን ብያኔ ይዘው እናገኛቸዋለን።

በመጀመሪያ ደረጃ ኢሬቻ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በመገንዘብ ወደ ርዕሰ ጉዳያችን እንሂድ።

**ኢሬቻ**

ኢሬቻ የምስጋና (ዋቃ) በዓል ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም ላሸጋገረው አምላክ ምስጋና የሚያቀርብበት ታላቅ በዓል ነው። ይሄን ስላደረግህልኝ፣ ከክረምት ወደ በጋ (ብራ) ስላሸጋገርከኝ አመሠግናለሁ እየተባለ ፈጣሪ የሚመሰገንበት የአደባባይ በዓል ነው።እሬቻ የዘመን መለወጫ በዓልም ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ክረምቱ በማለፉ በኢሬቻ ቀን ምስጋናውን ለፈጣሪ ያቀርባል።

ማኅበራዊ ደረጃ እና የእድሜ ልዩነት ሳይፈጠር፤ እስልምና፣ ክርስትና፣ ዋቄፈታ ሳይባል የኦሮሞ ሕዝብ በጋራ የሚያከብረው በዓል ነው። ለክርስቲያንና ለሙስሊም፤ እንዲሁም ለዋቄፈታዎች የእኩልነትና የአንድነት በዓል ነው።ምናልባትም ሁሉም ሃይማኖቶች በተናጠል ከነበራቸው የምስጋና ጊዜና እለት በአንድነት የሚገናኙበት ባህላዊ የምስጋና ሥርዓት ኢሬቻ ብቻ ነው።

"'ፈጣሪያችን ሆይ አንተ ያጸደቅከው ነው አብቦ ፍሬ ያፈራው፤ ለዚህም እናመሰግንሃለን" በማለት እርጥብ ተይዞ ይወጣል፤ ፈጣሪም ላደረገውም ሁሉ ይመሰገናል።

ኢሬቻ የኦሮሞ ማኅበረሰብ የይቅርታና የመልካም ምኞት መገለጫ እሴት ነው። ኢሬቻ ትልቅ የወንድማማችነት መሠረት የሚጣልበት፣ የተጣሉ ይቅር የሚባባሉበት በዓል ነው። የተጣላ ታርቆ፣ ቂሙን ትቶ በነጻ ልቦና ፈጣሪ ንጹሕ ወዳደረገው የውሃ አካል ይሄዳል። ኢሬቻ ቀልብ የሚነጻበት ቦታ ነው።

የመስቀል /ጉባ/ በዓልን ተከትሎ የሚከበረው ኢሬቻ


ፎቶ፡- ሐዱሽ አብርሃ

የቢሾፍቱ የሆራ አርሰዲ የ2014 ዓ.ም በዓል



የአዲስ አበባ የ2014 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል አከባበር

በፈጣሪና በፍጥረት መካከል ያለውን መስተጋብር የሚያጠናክር የገዳ ሥርዓት ፍልስፍና አካል ሲሆን፤ የኢትዮጵያውያን ሁሉ የጋራ ሀብት፤ የጋራ እሴት፤ የጋራ ቅርስ ነው።

**አከባበር**

የኢሬቻ በዓል ከገዳ ሥርዓት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ሲሆን በኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ ለዘመናት ሲከበር መቆየቱን ጥናቶቹ ያሳያሉ።

ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖቶች መስፋፋትን ተከትሎ የገዳ ሥርዓትም ሆነ የኢሬቻ ክብረ በዓል እየተቀዛቀዘ መጥቶ ነበር ይላሉ። በአሁኑ ወቅት ግን እየተጠናከረ ከኢትዮጵያ ባሻገር በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ የኦሮሞ ብሔር አባላት እያከበሩት ይገኛሉ።

በዋናነት ግን በኢትዮጵያ በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ ሆራ ፊንፊኔ፤ በቢሾፍቱ ከተማ ደግሞ የሆራ ሃር-ሰዲ ከመስቀል በዓል በኋላ ባሉት ቅዳሜ እና እሁድ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ በታደመበት በዓሉ ይከበራል።

የኦሮሞ ሕዝብ ምድር እና ሰማይን ለፈጠረው ፈጣሪው ዋቃ ምስጋናውን ለማድረስ፤ ለመላው የሰው ልጅ ሰላምና ደኅንነት ፈጣሪውን ለመለመን የኢሬቻ በዓልን ያከብራል። ዋቃንም ያመሰግናል።

ቂምና በቀል፣ አለመግባባትና ጥላቻ ያለው ማንኛውም ግለሰብ ጥላቻውን ሳይሽር፣ እርቅ ሳያወርድ፣ የገደለ ሳይክስ፣ እጁ ንፁህ ያልሆነ ግለሰብ ወደ ኢሬቻ ክብረ በዓል አይሄድም።

... ኢሬቻ ከመድረሱ በፊት አባ ገዳዎች በየአካባቢያቸው፤ በየደረጃው ባለው መዋቅር ያሉትን ችግሮች ይፈታሉ። የተጣላውን ያስታርቃሉ፤ የገደለ እንዲክስ ያደርጋሉ።ይህም የሚሆነው ኢሬቻ ካለው እሴት መካከል ሠላምና እርቅ አንዱ ስለሆነ ነው።ስለዚህ የኢሬቻ ዕለት ሠላም ይታወጃል፤ ይወደሳል።በኢሬቻ በዓል ስለሠላም ይሰበካል።ከቤተሰብ፣ ከጎረቤት፣ ከሰፊው ሕዝብ፣ ከፈጣሪና ከፍጡር ጋር በሠላም አብሮ መኖር እንደሚገባ ይታወጃል።

የኢሬቻ ስፍራ እርቅ የሚታወጅበት ስፍራ ነው።የኢሬቻ በዓል የፈጣሪና የፍጡር እርቅ የሚለመንበት ስፍራ ነው።የኢሬቻ ስፍራ ማኅበረሰቡ ስለጥፋቱና ስለበደሉ ፈጣሪውን ይቅርታ የሚጠይቅበት የእርቅ ስፍራ ነው።ሳያስቡ የተጋጩ ሰዎች እንኳን እርቅ የሚያወርዱበት ነው።ስለዚህ እሬቻ የእርቅና የአምላክ ምህረት የሚወርድበት ስፍራ ነው።ኦሮሞ በአባባሉ «Yoo namni walitti araarame, Waaqnis namaaf araarama» «ሰው እርስ በርሱ ከታረቀ እግዚአብሔርም ይታረቃል» የሚለው ለዚህ ነው።

**ሥነሥርዓቱ**

በነገው እለት ከማለዳው ጀምሮ ለዚሁ ክብረ በዓል ሲባል በተዘጋጀው አነስተኛ የተከተረ ውሃ ወይም ሆራ ፊንፊኔ በአባ ገዳዎች ምርቃትና የደስታ መልዕክት ተጀምሮ በድምቀት ይከበራል ተብሎ እየተጠበቀ ሲሆን፤ ከተለያየ የኦሮሚያ አካባቢዎችና ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሰባሰበ የበዓሉ እድምተኛ ልዩ ልዩ የኦሮሞ ባህላዊ አልባሳትን በመልበስ፣ ኅብረ-ዝማሬዎችን በማሰማትና በመጨፈር ሥርዓተ በዓሉን በደስታ ለማክበር ወደ አዲስ አበባ ይገባል።

የአከባበር ሥነሥርዓቱን በተመለከተ ያሉት ጥናቶች እንደሚያሳዩት "በዚህ የምስጋና ቀን፤ ወደ ኢሬቻ ሲኬድ ለምለም ሳር እና አደይ አበባ ተይዞ ነው።እነዚህ የራሳቸው ትርጉም ሲኖራቸው፤ ለምለም ሳሩ ዋቃ (አምላክ) የለገሰውን ልምላሜ ተምሳሌት ሲሆን፤ የአደይ አበባው ደግሞ፤ አብቦ ያለውን የእህል አበባንና የፍካት ተምሳሌትነት ይኖራቸዋል።በነዚህም ፈጣሪውን ወይም ዋቃን እንደ ለምለም ሳሩ ልምላሜን ስጠን፤ ያንተ የፍካት ኃይል ከኛ ጋር ይሁን ብለው፤ ይለምኑታል፤ ያመሰግኑታል።

ወደ ሐይቅም በመውረድ በእጅ የያዙትን ሳር በመንከር ግንባር እያስነኩ ሁለት ነገር ይደረጋል።አንደኛው ምስጋና ማቅረብ ሲሆን፣ ሁለተኛው ለቀጣዩ ፀሎት ማቅረብ ነው።በዚህ ሥርዓትም ከጨለማው ክረምት ወደ ብርሃን በሠላም ላሸጋገረ አምላክ (ዋቃ) ምስጋና ይቀርባል።የዘራውን እህል ስላበቀለለት ያመሰግናል።ዛሬን በሰላም እና በጤንነት ለመድረሱ ካመሰገነ በኋላ፤ ዓመቱ የሠላም፤ የብልፅግና፤ የጥጋብ እና የስኬት፤ እንዲሆንለትም ይለምናል።የጠፋን ፈልግልን፤ የታመመን ማርልን፤ የታሰረን ፍታልን ... በማለት ዋቃን ይለምናል፤ ይመርቃል፡፡"

ዝግጅቱን አስመልክተው እየተለቀቁ ያሉት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በበዓሉ ላይ የተለያዩ ብሔረሰብ ተወካዮችም የሚታደሙ ሲሆን፤ ይህም በከፍተኛ ደረጃ የሥነ ሥርዓቱ ድምቀት እንደሚሆን ይጠበቃል።

ከአዲስ አበባው ቀጥሎ ኢሬቻ በሆራ ቢሾፍቱ የሚከበር ሲሆን፤ በዛ በኩልም አስፈላጊው ዝግጅት ሁሉ መጠናቀቁን የከተማው አስተዳደር አስታውቋል።

የቢሾፍቱ ከተማ ምክትል ከንቲባ አቶ አብዱልሰላም መሐመድ፣ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር አድርገውት በነበረው ቆይታ እንደገለፁት በዓሉን ለመቀበል በሁሉም ዘርፍ በቂ ዝግጅት ተደርጓል። ኅብረተሰቡን በማስተባበር ከተማውን ውብና ጽዱ የማድረግ ሥራ በስፋት እየተከናወነ ይገኛል። ሰላምና ፀጥታን በተመለከተ የፎሌና የጸጥታ አካላት በቂ ዝግጅት እንዳለ ሆኖ ሕዝቡም ሰላሙን ለማስጠበቅ የተለመደውንና አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ላይ ሲሆን፤ ኅብረተሰቡን ለማገዝም የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ እየተሠራ ይገኛል።

በዓሉ በሰላም ተከብሮ በሰላም እንዲጠናቀቅ አስፈላጊው ሁሉ ተደርጓል። እንግዶች እንዳይጉላሉ የሚያደርጉ ቅድመ ዝግጅት ሥራዎችም በሙሉ ተሠርተዋል።

ከላይ እየተመለከትን እንደመጣነው፣ የኢሬቻ ስፍራ የሚለቀስበት፣ የሚረጋገሙበት፣ የሁካታ ስፍራ ሳይሆን በንጹሕ ልቦና፣ ከቂምና ጥላቻ ውጭ ፈጣሪ የሚለመንበት ወይም የሚመሰገንበት ስፍራ ነው።ኢሬቻ ያጡትን ነገር ወይም የተቸገሩበትንና የተጨነቁበትን የሚለምኑበት፤ ላገኙት ወይም ለተደረገላቸው ደግሞ አንዱ ፈጣሪ (WAKKA)ን የሚያመሰግኑበት ስፍራ ነው።ባጭሩ፣ የምስጋና እና ምልጃ ስፍራ ነው።በመሆኑም ሥነሥርዓቱ ሙሉ ሰላምን ይፈልጋል።

**ሰላምና ፀጥታ**

የኢሬቻ በዓላት ባህላዊ ይዘቱን በጠበቀ እና ሰላማዊ በሆነ መልኩ እንዲከበርም ሁሉም ማኅበረሰብ የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ እንደሚገባ፤ በበዓሉ ላይ ያልተገቡ ከትውፊቱ ያፈነገጡ ተግባራት እንዳይፈፀሙ፤ እንዲሁም የራሳቸውን የፖለቲካ አጀንዳ የሚያራምዱ ሰዎችን ለመከላከል በከፍተኛ ደረጃ እየተሠራ ሲሆን፤ ልክ እንደ መስቀል (ደመራ) በዓል ሁሉ፣ የኢሬቻ በዓልም በሰላም ተጀምሮ በሰላም እንዲጠናቀቅ (እንዲከበር) ሁሉም ኅብረተሰብ መረባረብ፣ መተባበርና ሰርጎ ገቦች እንዳይኖሩ መሠራት ያለበት መሆኑ በተለያዩ መድረኮችና መገናኛ ብዙኃን እየተነገረ ይገኛል።

የኢሬቻ በዓል ባህላዊ ትውፊትን ፣ የአብሮነትና የኢትዮጵያዊነት ስሜትን በጠበቀ መልኩ እንዲከበር ማኅበረሰቡ በመስቀል በዓል ላይ ያሳየውን ትብብር በድጋሚ ሊያሳይ ይገባል።የኢሬቻ በዓል እንግዳ ተቀባይነታችንን የምናሳይበት መሆን ይጠበቅበታል።

የደመራ በዓል በሰላም እንዲጠናቀቅ የኅብረተሰቡ አስተዋጽኦ ከፍተኛ የነበረ ሲሆን የኢሬቻ በዓልም በሰላም እንዲከበር እና ኅብረተሰቡ የተለያዩ ተልእኮዎችን ይዘው የሚመጡ ፀረ-ሰላም ኃይሎችን ዓላማቸውን ለማክሸፍ አንድ ሆኖ በአንድነት መቆም አለበት።

በአካባቢያችን ላይ የሚከሰቱ እንቅስቃሴዎችን በትኩረት በመከታተል በተለይም በዓሉ የኔ ነው በሚል መንፈስ ከሰላም ሠራዊት፣ ከጸጥታና ሌሎች ኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር በጋራ በመሆን በመስቀል በዓል ላይ የተገኘው ድል በኢሬቻ በዓል ላይም መደገም ይገባል፡፡

አባገዳዎች፣ ስንቄዎች እና ሌሎች ኅብረተሰብ ክፍሎች በሚገኙበት የዘንድሮ ኢሬቻ በዓል መስከረም 21 በአዲስ አበባ ሆራ ፊንፊኔ፤ መስከረም 22 በቢሾፍቱ ሆራ አርሰዲ የሚከበር መሆኑ ታውቋል።

**መልካም የኢሬቻ በአል!!!**

# ወጣቶች

## ‹‹ኢሬቻ ለኦሮሞ ሕዝብ የሰላም ምልክቱ ነው››

*አቶ ከድር እንዳልካቸው*
*የኦሮሚያ ክልል ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ*

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

የኢሬቻ በዓል ከገዳ ሥርዓት ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለው ይገለጻል።ገዳ ደግሞ ለኦሮሞ ማኅበረሰብ ምን እንደሆነ መናገር ለቀባሪው እንደማርዳት ነው።እናም በዚህ ውስጥ ሆኖ ብዙዎችን ያስተሳሰረው ኢሬቻ ለኦሮሞ ማህበረሰብ ብዙ ነገሩ ሆኖ ዘመናትን ተሻግሯል።ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ደግሞ በሁለት ቦታዎች ላይ በድምቀት የሚከበር በዓል ሆኗል።ክብረበዓሉ ከመስቀል በዓል በኋላ ባሉት ቅዳሜ እና እሁድ የሚከበር ሲሆን፤ በአዲስ አበባ ሆራ ፊንፊኔ፤ በቢሾፍቱ ከተማ ደግሞ ሆራ ሃር-ሰዲ እየተባለም ይከበራል።

ኢሬቻ በዚህ ውስጥ ግን በርካታ መሰናክሎችን ያሳለፈ የአደባባይ በዓል ነው።ማለትም በ2008 ዓ.ም ብዙዎችን ለሞት የዳረገ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ሆኖም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በአሉ በደመቀ ሁኔታ በመከበር ላይ ይገኛል፡፡የእርስ በእርስ ትስስርን ከማጎልበቱም በላይ ሀገራዊ አንድነትን በማጠናከር በኩልም በዓሉ የራሱን በጎ ጎን እያሳረፈ ይገኛል፡፡

ይህ አኩሪ በዓል ለራሳቸው የፖለቲካ ፍጆታ ለማዋል የተለያዩ ወገኖች ቢሞክሩም ኢሬቻ በየአመቱ እየደመቀና እየጎመራ ህዝብ በአል በመሆን ላይ ይገኛል፡፡ወጣቶችም በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ የበኩላቸውን ሲወጡ እየተስተዋሉ ነው፡፡የዘንድረውም የኢሬቻ በአለም ባህላዊ ትርፊቱን ጠብቆ እንዲከበር ወጣቶች እያደረጉት ያለውን ጥረት ምን መልክ እንዳለው ከኦሮምያ ክልል የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ እንዲሁም የኦሮምያ ወጣቶች ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ከድር እንዳልካቸው ጋር ቆይታ አድርገናል።እርሳቸው ያሉንንም እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢሬቻ ማለት ምን ማለት ነው፤ አገራዊ አንድምታውስ ምንን ያመላክታል?**

**አቶ ከድር፡-** ኢሬቻ እንደ ኦሮሞ ማህበረሰብ በርካታ ትርጉሞች የሚሰጡት በዓል ነው።ለአብነት ኢሬቻ የምስጋና በዓል ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ምድር እና ሰማይን ለፈጠረው ፈጣሪው ዋቃ ምስጋናውን ለማድረስ የሚጠቀምበት ነው።ለዚህ ምክንያታቸው ደግሞ ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም መሸጋገራቸው ነው።ከጨላማው ማለትም ከክረምቱ ወደ በጋው ወይም ብርሃኑ በመሻገራቸው በዓሉን መሰረት አድርገው አምላካቸውን ያመሰግኑበታል።

ኢሬቻ ማለት ዋቃ (ፈጣሪ) የፈጠረውን ማመስገን እንደማለትም ይወሰዳል።ስለዚህም ይህንን በዓል እድሜ ገደብ ሳይኖር፣ መልክና ቁመና ሳይወስን ፤ የገንዘብ መጠን ልዩነት ሳይደረግበት፤ ባለስልጣኑ ከተገዢው ሳይለይ ሁሉም በእኩል ደረጃ የሚያከብረውና ለአምላኩ ምስጋና የሚያቀርብበት ነው።

በሌላ በኩል ኢሬቻ የዘመን መለወጫ በዓልም ተደርጎ ይወሰዳል።የኦሮሞ ሕዝብ ክረምቱ በማለፉ በኢሬቻ ቀን ይደሰታል።ምክንያቱም በክረምት ወራት ተራርቆ ሳይገናኝ የቆየ ዘመድ አዝማድ መስከረምን አሳቦ ይገናኛል። ሕዝቡም ክረምቱን ስላሳለፍክልንና አዲስ ዘመንን ስለሰጠኸን እናመሰግንሃለን ይሉበታል።

ኢሬቻ የሰላም እና እርቅ ቀንም ነው።የኦሮሞ ሕዝብ ፈጣሪውን እያመሰገነ ለመላው የሰው ልጅ ሰላምና ደኅንነት ከፈጣሪው ይለምንበታል።ልመና ደግሞ የሚከናወነው በንጹህ ልብ በመሆኑ በወቅቱ የተጣላ መታረቂ ግድ ነው። ሰላም ማውረድ ውዴታ ሳይሆን ግዴታ ነው።እናም ተበዳይ ሳይቀር ቂሙን ትቶ በነጻ ልቦና ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት ዕለት ነው።

አንዳንዶች ደግሞ ኢሬቻ ማለት መስማማት፣ አንድነት፣ እርቅ ማለት ነው ይሉታል። ይህ ምሳሌነቱ ደግሞ አገራዊ አንድምታውን በሚገባ ያሳየናል።ምክንያቱም ኢትዮጵያዊነት ተስማምቶና ተግባብቶ መኖር ነው፤ ኢትዮጵያዊነት አብሮ መብላትና ተሰባስቦ መደሰት ነው።ኢትዮጵያዊነት ይቅር ባይነት፤ በፍቅር መኖርም ነው።ያለው የሌለውን ደግሞ የሚያሻግርበት፤ ችግርን በአብሮነት ለመፍታት የሚረባረብበትም ነው።ስለዚህም የኢሬቻን አገራዊ አንድምታ በዚህ ውስጥ እንመለከተዋለን ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡-ኢሬቻን ባህላዊ ነው፤ መንፈሳዊም ነው፤ ኑሮም ይሆናል ይባላል።ምክንያቱ ምንድነው?**

**አቶ ከድር፡-** ምክንያቱ በአንድ ነገር ብቻ የሚገለጽ አይደለም።በስርዓትና በአተገባበር ጭምር



የሚብራራ ነው።ለአብነት ኢሬቻ የምስጋና ቀን ነው ስንል መንፈሳዊነቱን በደንብ ያሳየናል። ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ራሳቸውን የማይገዙ ሰዎች በኢሬቻ ክብረ በዓል ላይ ይታረማሉ።ምክንያቱም ወደቦታው ለማምራትና አምላካቸውን ለመለመን ሲያስቡ የተጣሉትን ይታረቃሉ፤ ክፉ መንፈሳቸውን አራግፈው ንጹህ ልቦናቸውን ይዘው ይመጣሉ።

ወደ ባህላዊነቱ ስንመጣ ደግሞ ኢትዮጵያዊነቱ ከቡና አፈላሉ ይጀምራል።አዲስ የደረሰ የባቄላና የአተር እሸት ተቆልቶ ለቡና ቁርስ ይቀርብበታል። የአኮሌ ስርአት ማለትም ለመጀመሪያ ጊዜ የወለዱ ከብቶችን ለመመረቅ የሚከበር ስርአትም በዚህ ውስጥ ይከናወናል።ጊደሮች ወተታቸው ተጠራቅሞ፣ ግማሹ ተንጦ፣ ቅቤው ወጥቶ፣ ግማሹ እርጎ፣ ግማሹ አይብ ተደርጎ ቅንጬ ተሰርቶ፣ ዘመድአዝማድ ተሰብስቦ ከተመረቀ በኋላ ይበላል።.በዚህ ውስጥ ደግሞ መሰባሰቡ፣ ደስታን መጋራቱ፣ አዲስ ሰብልና ወላድ መመስገኑ፤ መልካሙን ነገር አብሮ መጋራቱ በሙሉ ባህል ነው።

ኢሬቻ ማለት ማምለክ እና ማመስገን ማለት ነው የሚሉም አሉ።ይሄን ስላደረግህልኝ፣ ከክረምት ወደ በጋ (ብራ) ስላሻጋገርከኝ አመሠግናለሁ እየተባለ ፈጣሪ የሚመሰገንበት ነው።ኢሬቻ ሠፊ አገልግሎቶች አሉት።መነሻውም በጣም የራቀ ነው።ለአብነት በእርጥብ ሣር ይወከላል።ይህ ማለት ደግሞ ኢሬቻ የልምላሜ ነጸብራቅ ነው።ሊጋብቻ ጥያቄ ሳይቀር እርጥብ ሣር ለአገልግሎት የሚውለው ለዚህ ነው።

ሌላው ኢሬቻ የምትለዋ ቃል የምትወክለው ሣር ወይም አበባን እንደሆነም ይነገራል።ምክንያቱ ደግሞ መልካም ነገር አብሳሪነትን የሚያስረዳ ነው።በኦሮሞ ባህል እርጥብ ሳር የያዘ ሰው ኢሬቻ የሚሄድ ሰው ነው።ለጋብቻ የሚጠይቅ ሰው ሳይቀር እርጥብ ሳር የሚይዘውም ከዚህ የተነሳ ነው።ስለዚህም ይህም ባህል ነው።እድምተኞቹ “መሬሆ” የሚለውን የምስጋና መዝሙር በአንድነት እያሠሙ ለአምላካቸው ምስጋና የሚያቀርቡበትም ሌላው ባህላዊ ክዋኔ ነው።በተመሳሳይ ህዝቡ የፈለገውን ባህላዊ ጭፈራ እየጨፈረ የሚያከብረውም ባህል ነው፡፡

ኢሬቻ ኑሮው ነው ሲባል በሚከበርበት ጊዜ ብቻ ማየት ይቻላል።ሁለት ጊዜ በዓሉን ወዶ ያከብረዋል።የመጀመሪያው መልካ (በውሃ አካል ዳርቻ) የሚከበረው ሲሆን፤ የምስጋና በዓሉም ነው።ለተደረገለት ሁሉ አምላኩን ያመሰግናል።ሁለተኛው በዓመቱ አጋማሽ ላይ የሚከበረው ሲሆን፤ ኢሬቻ ቱሉ (በተራራማ ቦታ) የሚከበረው ነው። ይህ በዓል ደግሞ የኦሮሞ ሕዝብ ፈጣሪውን የሚለምንበት ነው። በበጋው የፀሐይ ሃሩር ሰው እና ከብት በሚቃጠልበት ጊዜ ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘንብ የኦሮሞ ሕዝብ ወደ ተራራ ወጥቶ ፈጣሪውን ይለምናል። ይህን ተራራ የፈጠርክ ፈጣሪ ወቅቱን የሰላም አድርግልን፣ የሰላም ዝናብ አዝንብልን፣ ጎርፍን ያዝልን፣ የተዘራው ፍሬ እንዲያፈራ እንለምንሃለን" ይላል።ይህንን ተከትሎም ኢሬቻ ባህላዊ ነው፤ መንፈሳዊ ነው አለያም ኑሮው ነው እንዲባል አስችሎታል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢሬቻ ለኦሮሞ ምኑ ነው?**

**አቶ ከድር፡-** ኢሬቻ ለኦሮሞ ሕዝብ የሰላም ምልክቱ ነው።አምላኩን ማመስገኛው፤ ከአገሬው ሰው ጋር መገናኛው፣ ደስታውን መግለጫው፤ ቂምና በቀልን መርሻው፣ በአዲስ ተስፋ ቀጣዩን ዘመን መመልከቻው በአጠቃላይ ተስፋውን ለማለምለም የሚነሳበት በዓሉ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ አኳያ ኢሬቻ በኦሮሞ ወጣቶች ዘንድ እንዴት ይታያል?**

**አቶ ከድር፡-** ከወጣቶች ምልከታ አንጻር ኢሬቻን በብዙ በኩል መተንተን ይቻላል።ከገዳ አንጻር ብቻ ብናነሳው በርካታ ባህላዊና ትውፊታዊ የሆነ መልዕክትን ያዘለ ነው።ማለትም በየደረጃው የተለየ ተልዕኮ አለውና በዚያ ውስጥ የሚማራቸውን ነገሮች የሚተገብርበት በዓል ነው።ለምሳሌ ፎሌነቱ የእድሜ እርከኑን ብቻ ሳይሆን አብሮ የሚሰጠው ተልዕኮም አለው።ኢሬቻም እንዲሁ ከዚህ የተቀዳ ነገር ስለሆነ ብዙ ነገር እንደሚሰጠው ያውቃል።እናም ኢሬቻ በወጣቱ ዘንድ የሚታየው ራስን መግዢያው፤ እርቅን ማበልጸጊያው፤ ባህሉን ማጎልበቻው፤ አዲስ ተስፋውን ማያው፤ አምላኩን ማክበሪያው ነው።

ከዚያ ባሻገር ወጣቱ ለኢሬቻ ሲወጣ ነጻና በፍቅር ተሞልቶ ስለሚሆን በዓሉን የአንድነት፣ የመቻቻልና የሰላም ተምሳሌት እንደሆነ ያረጋግጣል።ሌላው ኢትዮጵያዊነቱን የሚያይበት መድረክም ስለሆነ አብዝቶ አገሩን እንዲወድ የማድረጊያ በዓል እንደሆነም ያስባል።የማህበረሰቡ አንድ አካል በመሆኑ ማህበረሰቡ የሚሰማውን ሁሉ ያደርጋል፤ ይኖርበታልምም።የሚሰማውም ይኸው አይነት ስሜት ነው።ምልከታውም ቢሆን ከዚህ የተለየ አይደለም።አውራ በዓሉ አድርጎት ያከብረዋል፤ ያስቀጥለዋልም።

**አዲስ ዘመን፡- ህወሓት መራሹ ስርዓት በኦሮሞ ህዝብ ላይ ሲያደርሳቸው የነበሩ ግፎችና በደሎች እንዴት ይታወሳሉ?**

**አቶ ከድር፡-** ይህንን በቃላት መግለጽ እጅግ ከባድ ነው።ምክንያቱም ህወሓት በሰው ልጅ ላይ ቁማር የሚጫወት ጨካኝ ቡድን ነው።ፖለቲካ ጥቅሙን እንጂ ማንንም የማያስቀድምም ነው።በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ያደረሰው በደልም በዚህ ደረጃ የሚገለጽ ነው።ሥራው አገር ማፍረስ ስለሆነም ባህልን ሲያጠለሽ፣ የተሳሳቱ ትርክቶችን ሲያሰፋና ሕዝብን ከሕዝብ ፣ማህበረሰብን ከማህበረሰብ ሲያጋጭ ኖሯል።አሁንም ከድርጊቱ አልተቆጠበም።ተደጋጋሚ ጦርነቶችን የምናየውም በዚህ ምክንያት ነው።በአጠቃላይ እርሱ ሰላም ጠል ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- በ2008 ዓ.ም በቢሾፍቱ በነበረው ኢሬቻ ክብረ በዓል ላይ በነበረው የኢህአዴግ ስርዓት አማካኝነት በርካታ ሰዎች ህይወታቸው አልፏል። ያን አሰቃቂ ጊዜ እንዴት ያስታውሱታል?**

**አቶ ከድር፡-** በሌሎች አገሮች አይደለም እንደዚህ አይነት መልካም ነገር መስበኪያ በዓላት የሌላቸውን እንኳን ፈጥረው ለሌሎች ለማሳወቅ ይጥራሉ።የሌላቸውን ታሪክ ታሪክ አለን በማለትም ገንዘብ ያደርጉታል።እኛ ጋር ግን እነዚህ በዓላት የጸብ ምንጭ ሲሆኑ ይስተዋላሉ።ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ አንድ ነው።ጠላት ማለትም እንደ ህውሓትና ሸኔ አይነቶች ገንዘባቸውን የሚያገኙት ታሪክን በማጥፋት፣ የሕዝብን ሰላም በማደፍረስ ነው።ስለዚህም መልካሙን በዓሎቻችንን ለራሳቸው ጥቅም ያውሉታል።ብጥብጥ አስነስተውም ይህንን አድርገናል ይሉበታል።የ2008ቱም የሆነው ይኸው ነው።

የኦሮሞን ሕዝብ ተሰባስቦ በዓሉን በሰላም እንዳያከብር የመስበርና የማሸማቀቅ ሥራ ለመሥራት ሞክሯል።ግን ሕዝቡ በቀላሉ የሚሰበር አይደለም፤ የሚሸማቀቅም እንዲሁ።ብዙ መስዋዕትነት ቢከፈልም ኢሬቻ በደመቀ መልኩ እንዲከበር አድርጎታል እንጂ።

ሕወሓትም ሆነ ኦነግ ሸኔ አሁንም ይተኛሉ ተብሎ አይታመንም።መሞከራቸው አይቀርም።ነገር ግን መቼም አይሳካላቸውም።በዓሉን ለማጠልሸት እንደ ገቢ ምንጭ እድሉ እንዲጠቀምበት ማንም አይፈቅድለትም።ምክንያቱም በሥራቸው ዛሬ ሁሉም አውቋቸዋል፤ ነቅቶባቸዋልም።ስለዚህም ነቅቶ እንደሚጠብቃቸው እርግጠኛ ነኝ።በተለይም የኦሮሞ ሕዝብ ይህንን እንዲያሳካ መቼም አይፈቅድለትም።ወጣቱም ቢሆን በዚህ ደረጃ ተዘጋጅቷል።ሰላምን ለማይፈልግ ሰው ማንም ቦታ አይሰጠውም።

**አዲስ ዘመን፡- በአጠቃላይ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ስቃይና መከራ ሲዘሩ የነበሩ ሰዎች አሁን የኦሮሞ ህዝብ ጠበቃ ሆነው ቀርበዋል፡፡ለእነዚህ አካላት የምታስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው?**

**አቶ ከድር፡-** የሀሰት ፕሮፓጋንዳው ገና ከመስቀል በፊት የጀመረ ነው።ይህ ደግሞ የአደባባይ በዓላትን የማጠልሸትና እንዳይከበሩ ማድረግ ላይ ያተኮረ ነው። ነገር ግን የመስቀል በዓል ምንም አይነት ችግር ሳይፈጠርበት በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በኦሮምያ ክልል ጭምር በመጡ ወጣቶች ሥራ በሰላም እንዲጠናቀቅ ሆኗል።ኢሬቻም ይህንኑ አይነት አከባበር ይኖረዋል።ይሁን እንጂ የማህበረሰቡ ርብርብ ግድ ያስፈልገዋል።የመጀመሪያው የሀሰት ወሬዎችን አልሰማም ማለት ሲሆን፤ ሌላው በነቂስ ወጥቶ የበዓሉ ድምቀት መሆን ነው።

ጠላት የሚመጣው አገር ወደድና የኦሮሞ ተቆርቋሪ መስሎ ነው።ይህንን የሚያወጣው ደግሞ አስተባባሪው ብቻ ሳይሆን ምልከታው ሰፊ የሆነው ሕዝብ ነው።ስለዚህም ሁሉም ሰው በመተባበር ይህንን የሰላም ምልክት የሆነ በዓል በሰላም እንዲጠናቀቅ ሊያደርገው ይገባል።የበአሉ ታዳሚዎች ልዩ እንቅስቃሴዎችን ካዩ ለጸጥታ አካሉ ወይም ለተመረጡት ፎሌዎች ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።የጥፋት ኃይሎችን ሀሳብ ላለማስፈጸም መጣር ይገባልም።ይህንን አይነት ተግባር እንፈጽማለን የሚሉም ቢሆኑ ለማንም የሚጠቅም ተግባር አይደለምና ከድርጊታቸው ሊቆጠቡ ይገባል። ኢሬቻ ለፊንፍኔ ስጋት ሳይሆን ትልቅ የገቢ ምንጭና ውበት ስለሆነ እንደ አገር ጥቅም አስቦ መስራቱ ለሁሉም ሰው ያገለግላል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢሬቻ በሰላም እንዲጠናቀቅ በኦሮምያ ወጣቶች ማህበር ዘንድ ያለው ዝግጅት ምን ይመስላል።በተለይም ሰላም ከማስከበርና በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ከማድረግ አኳያ?**

**አቶ ከድር፡-** ይህ በዓል ሌሎች ክልሎች ብቻ ሳይሆኑ ከጎረቤት አገር ጭምር ሰዎች መጥተው የሚታደሙበት ነው።ሰፊውና ብዙ ሕዝብ ያለበት የኦሮምያ ክልልም ታላቅ በዓሉ ስለሆነ ይታደምበታል።ስለዚህም በርካቶችን ሰብስቦ የሚያወዳጅ በመሆኑ በርካታ በርካታ መስተጋብሮች ይኖራሉ።የመጡ እንግዶችን ጭምር በአግባቡ አስተናግዶ መመለስ ይገባል።ለዚህ ደግሞ አንድ ሺህ ፎሌዎችን መልምለን ተልዕኮ በመስጠት ዝግጅታችንን አጠናቀናል።

ከዚያ ባሻገር ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር ለመስራትም በእነርሱ በኩል ወጣቶች ተመልምለው ተዘጋጅተዋል።ስለዚህም በዓሉን በሰላም ለማጠናቀቅ በሁለቱም በኩል በቂ ዝግጅት ተደርጓል።ከጸጥታ አካሉ ጋርም በቅርበት ለመስራት መግባባት ላይ ተደርሷል።ይህ ደግሞ ቀደም ብሎ በመስቀል በዓልም የታየ ነው።ስለሆነም በኢሬቻም የሚደገም ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢሬቻ ሰላም እንደሆነ ማረጋገጥ ያለበት ወጣቱ እንደሆነ ይነገራል፡፡ከኢሬቻም በኋላ በርካታ በዓላት አሉንና የወጣቶች ሚና በምን መልኩ መታየት አለበት?**

**አቶ ከድር፡-** የአደባባይ በዓላት የገቢ ምንጭ፣ የውበት እና የማንነትን መግለጫ ናቸው።ጥቅሞቻችንን በምን መልኩ እንደምናገኝ የሚያመላክቱ አቅጣጫ ጠቋሚም ናቸው።ስለሆነም ወጣቱ ሊጠቀምባቸው ይገባል።በተለይም አፍላ እድሜ ላይ በመሆኑ የሥራ እድሎችን ጭምር ያይባቸዋል፤ ይሰራባቸውና ይለወጥባቸዋልም።በዚህ ውስጥ ደግሞ አገርን ማስጠራት ጭምርን ያመጣባቸዋል።እናም ጥቅሙ ብዙ ነውና ሁሉም መልካም ጎናቸውን አይቶ ካላቸው በረከት መቋደስ ይገበዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?**

**አቶ ከድር፡-** በዓላት የማንም ግለሰብ ወይም ብሔር ብቻ አይደሉም።የሁሉም ሕዝብ ናቸው።ይህንን ማስከበርና ማክበር ያለበትም አካል አንድ አይደለም።ሁሉም ለበዓሉ ስኬታማነትና በሰላም መጠናቀቅ የበኩሉን ማበርከት አለበት።ምክንያቱም ሰላማዊ የሆነ ክብረበዓል ሲኖር ሰውም አገርም ይጠቀማል።ስለዚህም ኢሬቻን ለማክበር ወደቦታው የሚሄደው ብቻ ሳይሆኑ በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ያሉ ለበዓሉ ልዩ ትኩረት ሰጥተው መስራት አለባቸው።ይህንን ካደረጉ ደግሞ ጎንለጎን የሚጠቀሙበትን ነገር ይዘረጋሉ።ለምሳሌ፡- ለበዓሉ የመጣው ታዳሚ በምግብና መሰል ነገሮች የከተማዋን ገቢ ከፍ ማድረግ ይቻላል።እናም ይህ እየታሰበ ለበዓሉ ስኬት ሁሉም በጋራ መሰራት ይኖርበታል።

**አዲስ ዘመን፡ ስለሰጡን ማብራሪያ እጅግ አድረገን እናመሰግናለን።**

**አቶ ከድር፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# የምድር በረከት

## የማእድን ሀብትን በጥናት ለይቶ በአቅም የመምራት ጥረት– በጉራጌ ዞን

ስምስም መንግሥቱ

በአስር አመቱ እቅድ ትኩረት ከተሰጣቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል የማእድን ዘርፍ አንዱ ነው። የማእድን ዘርፉን በማልማት ተጠቃሚ ለመሆን ሥራው በቀበሌ፣ ወረዳ፣ ዞንና ክልል እያለ እንደ ሀገር በተቀናጀና በተናበበ መልኩ እንዲከናወን የሚያስችል መዋቅር ተዘርግቶለታል ። ‹‹ጋን በጠጠር ይደገፋል›› እንደሚባለው በዘርፉ ውጤታማ ለመሆን እያንዳንዱ መዋቅር የየራሱን ድርሻ መወጣት ይጠበቅበታል ። እያንዳንዱ መዋቅር እንደ ሀገር የተያዘውን የዘርፉን እቅድ ማሳካት ከቻለ የዘርፉን አልሚዎች፣ ማእድኑ ያለበትን አካባቢ ማህበረሰብ ተጠቃሚነት ማረጋገጥና የሀገርን የኢኮኖሚ ማሳደግ ይቻላል ።

እስከ አሁን ካለው የዘርፉ እንቅስቃሴ መረዳት የሚቻለው ግን በዘርፉ አንዳንድ ለውጦች ቢመዘገቡም፣ የተዘረጋው መዋቅር ሁሉ በሚፈለገው መልኩ የማይገኝና ችግሮችን እየፈታ የማይጓዝ መሆኑን ተከትሎ በዘርፉ እንደሚጠበቀው ውጤታማ መሆን እንዳልተቻለ ነው። ለዚህም ማሳያዎቹ የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ የበጀትና የሌሎች አስፈላጊ ድጋፎች አለመሟላት ናቸው ። በክትትልና ቁጥጥር በኩልም ተመሳሳይ ችግር ይታያል ።

ዘርፉን በተመለከተ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች እንደሚሉት፤ የማእድን ሥራው የሚከናወነው ታች ሆኖ ሳለ፣ የማእድን ሀብቱም የሚገኘው በገጠራማው የሀገሪቱ ክፍል ሆኖ፣ በሥራው ቦታ ጠንካራ በሆነ አደረጃጀት ሥራዎች እንዲሰሩ አለማድረግ የዘርፉን እድገት ጎድቶታል፤ ሁኔታው ዘርፉን ለመምራት የሚያስችል አቅም እንዳይፈጠርም ምክንያት ሆኗል ።

ዘርፉ ለዜጎች የሥራ ዕድል በማስገኘት ኑሮአቸውን ለመለወጥ እንዲያስችላቸው ከማድረግ ባለፈ የማዕድን ውጤቶች ለዓለም ገበያ ውለው የውጭ ምንዛሬ ገቢ በማስገኘት፣ ከውጪ የሚመጡ ምርቶችን በመተካት የውጭ ምንዛሬ በማዳን የሀገር ኢኮኖሚን ከፍ ለማድረግ ያለው አበርክቶ የጎላ መሆኑን ተገንዝቦ ትኩረት ሰጥቶ አለመስራት ይስተዋላል፤ ስራው ብዙ የስራ እድል ሊፈጠርበት ሲገባ በጥቂት ተጠቃሚዎች ብቻ የሚከናወን መሆኑም ሌላው ክፍተት ነው ።

ማእድኑ ለሚገኝበት አካባቢ ማህበረሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያላቸውን ማእድናት በምርምርና ጥናት ለይቶና ሰንዶ ለመንግስትና ለአልሚዎች በማመቻቸት ረገድ ኃላፊነት ካለባቸው ተቋማት መካከል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ይገኙበታል ። ተቋማቱ በዘርፉ በየጊዜው ጥናትና ምርምር ቢያካሂዱም፣ የጥናትና ምርምር ሥራዎቹ መደርደሪያ (ሼልፍ) ከማድመቅ በዘለለ የፈየዱት የለም የሚሉ ጥቆማዎች ይደመጣሉ ።

የምርምር ውጤቶች ወደ ተግባር በመቀየር በኩል እስከታች የተዘረጋው የዘርፉ መዋቅርም የየድርሻውን በመወጣት ለአካባቢው ማህበረሰብ የስራ እድል በመፍጠር፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ማድረግ እና እንደ ሀገር የተያዘውን ጠንካራ ኢኮኖሚ የመገንባት ራእይን ማሳካት ይጠበቅበታል፤ ይሁንና በስራ አጋጣሚ በአንዳንድ አካባቢዎች ካለው ሁኔታ መረዳት እንደሚቻለው በማእድን ልማቱ ለመሰማራት እየሞካከሩ ያሉ ኩባንያዎችን በመደገፍ በኩል በተለይ በላይኛው መዋቅር በኩል ክፍተቶች ይስተዋላሉ ።

እኛም በዚህ ቅኝት እያንዳንዱ የቀበሌ፣ የወረዳና የዞን መዋቅር በማዕድን ዘርፍ በመንቀሳቀስ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት እያከናወነ ስላለው ተግባር በደቡብ ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጉራጌ ዞን ስላሉት የማዕድን አይነቶች፣ የማእድን ሀብቶቹ ጥቅም ላይ ውለው አልሚዎቹን እና የየአካባቢውን ማህበረሰብ እንዲሁም ሀገሪቱን ተጠቃሚ በማድረግ በኩል እየተከናወነ ስላለው ተግባር የጉራጌ ዞን ውሃ መስኖና ማዕድን ልማት መምሪያ ኃላፊ አቶ ፍሰሐ ዳምጠውን አነጋግረን እንደሚከተለው አቅርበናል ።

> **የምርምር ውጤቶች ወደ ተግባር በመቀየር በኩል እስከታች የተዘረጋው የዘርፉ መዋቅርም የየድርሻውን በመወጣት ለአካባቢው ማህበረሰብ የስራ እድል በመፍጠር፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ማድረግ እና እንደ ሀገር የተያዘውን ጠንካራ ኢኮኖሚ የመገንባት ራእይን ማሳካት ይጠበቅበታል፤**

አቶ ፍሰሐ እንደገለጹት፤ ጉራጌ ዞን ለግንባታ፣ለኢንዱስትሪና ለሌሎችም ግብአቶች የሚውል የማዕድን ሀብት በስፋት ከሚገኝባቸው የደቡብ ክልል ዞኖች መካከል ይጠቀሳል ።ለአብነትም በዞኑ የምሥራቅ ክፍል አካባቢ ላይምስቶን፣ግራናይት የመሳሰሉት የማዕድን አይነቶች፣በምዕራቡ ክፍልም ተመሳሳይ ሆነ ሀብት አለ፤ ከእነዚህም መካከል ለኢንደስትሪ በተለይም ለሲሚኒቶ ፋብሪካዎች ግብአት የሚውል የድንጋይ ከሰል፤ኖራ ድንጋይ፣ከከበሩ ማዕድናት ደግሞ ኦፓል ማዕድናት ይጠቀሳሉ ።

ለኢንደስትሪ ግብአት የሚውሉትን ማዕድናት ሀብት ክምችት በጥናት ለይቶ በተደራጀ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውል በክልሉ የተለያየ ድጋፍ ተደርጎ የዲላና ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲዎች ጥናት እንዲያካሂዱ ተደርጓል ። በጥናት ግኝቱም በተለያየ መንገድ ከሚታወቁት የማዕድን አይነቶች በተጨማሪ ሌሎች ማእድናት በዞኑ እንደሚገኙ ተረጋግጧል ። ተጨማሪ የጥናት ሥራዎችን የሚጠይቁ የማዕድን አይነቶች መኖራቸውም ተደርሶበታል ።

በተለይም በክልሉና በዞኑ መካከል በተደረገ የውል ስምምነት በክልሉና በዞኑ የማዕድን ባለሙያዎች በጋራ በተካሄደ ጥናት በመጀመሪያው ዙር በተከናወነ የናሙና ውጤት በዞኑ እኖር ወረዳ ውስጥ የወርቅ ማዕድን መኖሩን የሚያሳይ ምልክት ማየት ተችሏል፤ ነገር ግን ያለውን የወርቅ መጠንና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች እርግጠኛ ከመሆን በተጨማሪ በጥልቀት የጥናት ሥራ ማድረግ ያስፈልጋል ።

የከበሩ የጌጣጌጥ ማዕድናትንም በተመለከተም ኦፓል የሚባለው ማዕድን በዞኑ የምሥራቁ ክፍል በሶዶ፣ በምዕራቡ ክፍል ደግሞ በእኖር አካባቢዎች ስለመኖራቸው በተመሳሳይ በናሙና ጥናት ተረጋግጧል ።ተጨማሪ ጥልቅ የጥናት ሥራ የሚያስፈልገው የወርቅና የኦፓል ማዕድኖች የሚገኙባቸው በዞኑ የምዕራቡ አካባቢ ነው ።

የከሰል ድንጋይ ሀብትን በተመለከተም አቶ ፍሰሐ እንዳስረዱት፤ ማእድኑ በዞኑ በተለያዩ አካባቢዎች ቢገኝም፣ በተለይ በዞኑ አበሽጌ ወረዳ በሁለት ቀበሌዎች ውስጥ በስፋት ይገኛል ። በአበሽጌ ወረዳ በጊቤ ይበሬ ቀበሌ አስተዳደር በ2013ዓም በኢንዱስትሪ ማዕድን የድንጋይ ከሰል የምርመራ ፈቃድ የወሰደው ሰን ማይኒንግ የተባለው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ እስካሁን ወደ ሥራ አለመግባቱ ልማቱን ከማጓተቱም በላይ ሁለት ቀበሌ የሚሆን ሰፊ ቦታ አጥሮ መያዙ ጉዳቱን የከፋ አድርጎታል ።

ወደ ልማቱ ባለመገባቱም የአካባቢው ማህበረሰብ ቅሬታውን እየገለጸ ይገኛል ። ኩባንያው ወደ አካባቢው ሲመጣ ልማቱ ወደፊት የሚያስገኘውን ጥቅም ታሳቢ በማድረግ ማህበረሰቡ ደስታውን መግለጫም እርድ አከናውኖ ነው ኩባንያውን በበጎ የተቀበለው ። የኩባንያው ወደ ስራ አለመግባት ግን የማህበረሰቡን ተስፋ አመንምኖታል ።

ችግሩን የተገነዘበው ክልሉ ለኩባንያው ፍቃድ ለሰጠው የማዕድን ሚኒስቴር በጽሁፍ ቢያሳውቅም፣ እስካሁን የተወሰደ እርምጃ ግን የለም ። ዞኑም ሆነ ክልሉ የኩባንያውን ፈቃድ መሰረዝ ባለመቻሉ እንጂ ፈጣን ውሳኔ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው ።

ሌሎች በከሰል ማልማት የምርመራ ፈቃድ ለመውሰድ ሁለት ኩባንያዎች በሂደት ላይ ይገኛሉ ። በነዚህ ኩባንያዎችም ላይ ተስፋ ተጥሏል ። ደቡብ ሶዶ በሚባለው ወረዳ ላይ ከሁለት ወር በፊት አንድ ኩባንያ በይፋ ተመርቆ ወደ ማምረት ሥራ ውስጥ ገብቷል ። ግራናይት በሚባለው ማዕድን አይነት ላይም በአበሽጌሌና ሶዶ ወረዳዎች ውስጥ ለማልማት ፍቃድ የወሰዱ ኩባንያዎች ወደ ሥራ ለመግባት በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ ።

በራስ አቅምና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጋራ ትብብር የጥናት ሥራ በዞኑ ውስጥ የማዕድን ሀብት ስለመኖሩ ከማረጋገጥ ባለፈ ሀብቱን ወደ ጥቅም በመለወጥ ላይ የሚሰራው ሥራ ሀብቱ አለ የሚባለውን ያህል እንዳልሆነ ይነገራል፤ የዚህ ምክንያቱ ምን ይሆን? ብለን ላነሳንላቸው ጥያቄ ከዞናቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አያይዘው ምላሽ የሰጡን አቶ ፍስሃ እንዳሉት፤ የጉራጌ ዞን ውሃ፣ መስኖና ማዕድን ልማት መምሪያ ዋና ተልእኮና ተግባር በዞኑ ያለውን የሀብት መጠን ወይንም አቅም መለየት ነው ። በዚህ ረገድ በተለይ በ2014 በጀት አመት ሰፊ ተግባር ተከናውኗል ። የዞኑና የክልሉ ባለሙያዎች፣የዲላና ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲዎች ጥናቶችን አካሂደዋል ።

እንደ አቶ ፍሰሐ እምነት በጥናት የመለየቱ ሥራ ቢከናወንም፣ ወደ ልማት የገቡ ኩባንያዎችም ቢኖሩም፣ በድምሩ የሚያሳየው ውጤት ወደፊት ሰፊ የቤት ሥራ መኖሩን ነው ።በተያዘው በጀት አመት ለውጤት የሚያበቃ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንደሚኖር እምነት አላቸው ።

ከነክፍተቶቹም ቢሆን ዞኑ እንደውጤት የሚጠቅሰው ነገር ይኖር እንደሆንም አቶ ፍሰሐ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ እንዳብራሩት፤ ዞኑ ለኢንዱስትሪ ግብአት በሚሆኑ ማዕድናት ላይ እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም በጅምር ደረጃ የሚጠቀስ እንጂ ስላስገኘው ጥቅም ለመናገር የሚያስችል አይደለም ። ይህ ሲባል ግን ተስፋው የተሟጠጠ አይደለም ።ለግንባታው ዘርፍ በሚውለው ማዕድን ላይ ግን ጥሩ የሚባል ሥራ ተሰርቷል ።

በማህበር ተደራጅተው ዘርፉ ላይ የሚሰሩ ወጣቶችንም ማፍራት ተችሏል ። የባለሀብቱ ተሳትፎም የተሻለ ነው ። በዚህኛው ዘርፍ ጥሩ የሚባል ነገር ቢኖርም ህጋዊ ሆኖ ከመሥራት ይልቅ ህገወጥነትን የመምረጡ ሁኔታ፣የአካባቢ ሥነመህዳርን ጠብቆ ለማምረት ያለው ፈቃደኝነት ማነስና በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈለገው ልክ ውጤታማ ባለመሆኑ የበለጠ መሥራት ይጠበቃል ።

የዞኑ የ2015 በጀት አመት የእቅድ የትኩረት አቅጣጫን በተመለከተም አቶ ፍሰሐ እንዳብራሩት፤ ከጥናትና ምርምር አኳያ የተጀመሩ ሥራዎች እንዲጠናቀቁና ውጤቱን ይፋ ማድረግ ያስፈልጋል፤ ይህም ስራውን በጋራ የሚሰሩትን ወላይታ፣ዲላና ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲዎችን ያካትታል ። ከማልማት አኳያም በተለይ ለግንባታ ግብአት የሚውሉ ማዕድናት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሀብት ክምችቱ በስፋት በሚገኝባቸው የዞኑ ወረዳዎች በትኩረት ለመሥራት በእቅዱ ተካትቷል። በግንባታ የማዕድን ዘርፍ በ2014 በጀት አመት ወደ 48 በመቶ የሚሆነው የአካባቢው ወጣት ተጠቃሚ መሆን የቻለ ሲሆን፣ በዚህ በጀት አመትም የበለጠ በመስራት ወጣቶቹን ተጠቃሚ ለማድረግ እንቅስቃሴው ተጠናክሯል ።

ያለፉ ክፍተቶችን አርሞ በመሙላት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብም ሆነ በእቅድ የተያዙትን ከግብ ለማድረስ የማስፈጸም አቅም ወሳኝ ነው፤ ከዚህ አንጻር ቢሮአቸው ከአደረጃጀት ጀምሮ ሥራውን በብቃት ለመወጣት የሚገኝበትንም በተመለከተ አቶ ፍሰሐ በሰጡት ማብራሪያ እንዳስታወቁት፤ የማዕድን ዘርፉን የሚመራ ክፍል ተደራጅቷል ።እሳቸው በሚመሩት መምሪያ ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎችና የሥራ ኃላፊዎች ያካሄዱት የሥራ ግምገማ የሚያሳየው የማስፈፀም አቅም ዝቅተኛ ሆኖ መገኘትን ነው ። ዘርፉ ላይ የሚገኙትን ባለሙያዎች ክህሎት ማሳደግ ይጠበቃል ።

በሥራ ሂደት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ወይንም ማነቆዎችን እንዲሁም መልካም ስለሚባሉት ተግባራትም አቶ ፍሰሐ ሲያብራሩ እንደገለጹት፤ የማስፈጸም አቅም ውስንነትን መቅረፍ ያስፈልጋል፤ ባለሙያዎች የጥናት ሥራዎችን ማከናወን እንዳለባቸው፣የታችኛውን መዋቅርም መደገፍ ከባለሙያው እንደሚጠበቅ እንዲሁም የሰው ኃይል መጨመር እንደሚያስፈልግ በሥራ ግምገማ ከተለዩት መካከል ይጠቀሳሉ ።

በዚህ መልኩ በተከናወኑ የማስፈጸም አቅምን የማሳደግ ተግባራት በ2015 በጀት አመት የተሻለ አፈጻፀም ለማስመዝገብ ይረዳል የሚል ተስፋ አሳድሯል ። በዘርፉ የሰለጠነ ባለሙያና የተሟላ ቴክኖሎጂ ቢኖር ግን የበለጠ ውጤታማ መሆን ይቻላል ። በአቅም ውስንነት ሳቢያ እነዚህን ማሟላት አለመቻሉ አንዱ ተግዳሮት ቢሆንም፣ በተቻለ አቅም ጥረት እየተደረገ ነው ። ከወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን አንዳንድ ሥራዎችን ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ነው ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲንም ቢጠየቅ ፈቃደኛ እንደሚሆን ጥርጥር የለም፤ ሁሉንም አማራጭ ማየት ግን ከአስፈጻሚው አካል ይጠበቃል ።

ዞኑ ከፌዴራል ማዕድን ሚኒስቴር ጋር ቀጥታ ግንኙነት ባይኖረውም ሚኒስቴሩ ፍቃድ የሚሰጣቸው ኩባንያዎች በዞኑ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው በዞኑ የማዕድን ዘርፉን የሚመራው አካል ሥራቸውን በመከታተል ያለውን ሁኔታ የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት የሚሉት አቶ ፍሰሐ፣ ፍቃድ ወስደው ወደ ሥራ የማይገቡ ኩባንያዎች አዲስ ኢንቨስትመንት ለመሳብ እንቅፋት መሆናቸውን ይገልጻሉ ። የኩባንያዎቹ ስራ አለመጀመር የአካባቢው አርሶ አደር ‹‹ቦታ ሊይዙብኝ ነው ። ሳያለሙ ለራሳቸው ሊጠቀሙ ነው›› የሚል ስጋትና ጥርጣሬ ሊያድርበት እንደሚችል ይጠቁማሉ ። የፌዴራል መንግስት ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ፈጣን ምላሽ ማግኘት እንዳለባቸው አስምረውበታል ።

በአጠቃላይ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሚገኘውን የማዕድን ሀብት በተመለከተ የሀብት ክምችት ይገኝባቸዋል በተባሉ በተወሰኑ የክልሉ ወረዳዎች ጥናትና ምርምር በማድረግ ባለፈው አመት ሲሰራ የቆየው ዲላ ዩኒቨርሲቲ የጥናት ውጤቱን ለሚመለከተው ክፍል ማስረከቡን በዚሁ አምዳችን ለንባብ ማብቃታችን ይታወሳል ። ጥናቱን መሠረት አድርጎ ወደተግባር መለወጥ የማዕድን ዘርፉን የሚመራው አካል ስልጣንና ኃላፊነት ነው ።

የምርምር ሥራውን በመምራትና በማስተባበር በቅርበት ሲሰሩ የነበሩት በዲላ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ክፍል ምክትል ፕሬዝደንት ዶክተር ደረጄ ክፍሌ እንደሚሉት፤ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ለክልሉ ያስረከበው የጥናት ሰነድ ወደ ሥራ ስለመለወጡ መረጃ ጠይቀው በዞን ደረጃ ዘርፉን የሚመሩ አካላት ስለጥናቱ መረጃ እንደሌላቸው መገንዘባቸውን ተናግረዋል ።

ዘርፉን የተመለከተ ማንኛውም መረጃ እስከታችኛው መዋቅር መድረስ ይኖርበታል፤ ላይ ብቻ የሚቀር ከሆነ ሥራውን ተናብቦ ለመሥራት ያስቸግራል ። ይሄ መታረም አለበት ያሉት ዶክተር ደረጄ፣ ዩኒቨርሲቲው ከአንድ ወር በፊት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ መድረክ ማካሄዱን ይገልጻሉ ። በመድረኩም በማዕድን ዘርፉ ባለፈው በጀት አመት የተከናወነውንና አፈጻጸማቸው፣ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት መጠናከር ያለበት መሆኑ እንዲሁም ቀጣይ የጋራ ሥራ አቅጣጫ መነሳቱን ያብራራሉ ። በቀጣይ እቅዳቸው ከዩኒቨርሲቲዎች የሚፈልጉትም ጭምር በሪፖርቱ መቅረቡን አመልክተዋል ።

ዲላ ዩኒቨርሲቲ የጥናት ውጤቱን ካስረከበ በኃላ ወደተግባር መለወጥ የነርሱ ተግባር እንደሆነ ቢገነዘብም ወደ ሥራ ለመግባት የሚያስችላቸውን ክህሎት እንዲያገኙ የማድረግ ኃላፊነቱን እንደሚወጣ የጠቀሱት ዶክተር ደረጀ፣ በተለይም ወደሥራው የሚሰማሩ ወጣቶች ሥልጠና እንዲያገኙ ዩኒቨርሲቲው ባለሙያ በመስጠት እገዛ አንደሚያደርግ ገልጸዋል ።በዩኒቨርሲቲው በኩል እንዲህ ያሉ ተግባራት በተከታታይ የሚከናወኑ መሆናቸውን አስታውቀው፣ የጥናትና ምርምር ሥራውም ቢሆን ዩኒቨርሲቲው በራሱ ከሚያከናውነው በተጨማሪ ክልሉ ፍላጎት ሲያቀርብ አብሮ እንደሚሰራ አስረድተዋል ።

እኛም ዞኑ ሀብቱን ለይቶ በአቅም ለመምራት እያደረገ ያለው ጥረት ሊበረታታ ይገባል እንላለን ።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## አንድ ዓይነት ልዩዎች

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

አባቴ ባርኔጣ ሲያደርግ አልወድም። አንድም ቀን ግን የአባቴን ራስ ያለባርኔጣ አይቼው አላውቅም። ተወልጄ እቅፉ ውስጥ ቦርቄ፣ ዩኒቨርሲቲ እስከላከኝ ቀን ድረስ አባቴን የማውቀው በባርኔጣ ነው። ለብሶና ዘንጦ በዛ ሽቅርቅርነቱ ላይ ባርኔጣውን ሲደፋ ሞገሱ ይሰወርብኛል። አባቴን ያለባርኔጣ ለማየት ያላደረኩት ጥረት የለም። ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ ከነባርሜጣው ነው የግቢያችንን አበባዎች ውሀ እያጠጣ የማየው። ማታም ከነባርሜጣው ብቻውን ትቼው አጠገቡ ላይ እንቅልፍ ያዳፋኛል። አባቴን ያለባርኔጣ እንዳየው ብዬ ጠዋት ከእንቅልፌ ነቅቼ ወደመኝታው ሄጄ አውቃለሁ.. ግን አይቀናኝም። ባርኔጣው ከጭንቅላቱ ጋር አብሮ የተሰፋ ይመስል ከነባርሜጣው አገኘዋለሁ። አንዳንዴ አብሬው ካልተኛሁ ብዬ አለቅስና አብሬው እተኛለሁ.. የአባዬን ሁኔታ ለማየት ብዬ እንቅልፍ እያዳፋኝ ብዙ እቆያለው..ግን መጨረሻውን ሳላይ በእንቅልፍ ተሸንፌ ራሴን አጠገቡ ተኝቼ አገኘዋለሁ። ጠዋት አጠገቤ መጥቶ ከእንቅልፌ የሚቀሰቅሰኝ ከነባርሜጣው ነው።

አንድ ቀን..ነፍሳባታችን ቤት መጡ። ሁላችንም መስቀል መሳለም ስለነበረብን በተዋረድ ቆምን። መጀመሪያ አባዬ ከዛ እማዬ ..ከእማ ቀጥሎ አጎቴ መጨረሻ ላይ እኔ ቆምኩ። የኔ አይን አባቴ ባርኔጣውን አውልቆ ነው ሳያወልቅ የሚሳለመው የሚለውን ማየት ነበር። እውነት ለመናገር እንደዛ ቀን አዲስ ነገር ለማየት የናፈኩበት አጋጣሚ አልነበረም። አባቴን በልቤም በነፍሴም ጠበኩት። ያን ቀን ዛሬም ድረስ በሚገርመኝ ሁናቴ አባቴን ያለባርሜጣ አየሁት። ባርሜጣውን አውልቆ ተሳለመ። አይኔን ከታች ወደላይ ኣሽቀንጥሬ ብርቅ የሆነብኝ የአባቴ ራስ ላይ እስካደርሳቸው ድረስ አባቴ የአባን መስቀል ስሞ ባርኔጣውን ጭንቅላቱ ላይ ደፋ። አይኔ ሜዳ ላይ ቀረ። ያ ቀን አባቴን ለአንድ ጊዜ..የምን ለአንድ ጊዜ አፍታ ለማትሞላ ቅጽበት ያለባርሜጣ ያየሁበት ቀን ሆነ። ያቺ ቀን አባቴን ያለባርሜጣ በማየቴ ብቻ የሕይወቴ አዲስ ቀን ሆና አለፈች። ዛሬም ድረስ የሕይወትሽ አዲስ ነገር ምንድነው ላለኝ ያን ቀን አባቴን ያለባርሜጣ ማየቴ ስል እመልሳለሁ። አባዬን ያለባርሜጣ ለማየት ስል ቄሱ እኛ ቤት በየጊዜው በመጡ ስል ስመኝ ነበር። ግን በዓመት አንድ ጊዜ ነበር የሚመጡት..ወይም እኔ ተኝቼ ባንቀላፋሁበት ቤታችንን ጸበል ለመርጨት ይመጣሉ። ያኔ በእናቴና በአባቴ ታጅበው ቀዝቃዛውን ጸበል ፊቴ ላይ ሲቻልሱት..ከእንቅልፌ እመነጠቃለሁ። አባዬን ቄሱ ፊት በጸበል ርሶ ሳየው..ባርሜጣውን እውልቆ የተሳለመባትን ቅጽበት ባለማየቴ እቆጫለሁ።

አባቴን ያለባርሜጣ የማየት ፍላጎቴ አልቆመም። ቀን በቀን በረታ እንጂ። አንድ ቀን አባቴ የበዓል ጠላ ጠጥቶ የሰከረበትን ቀን ጠብቄ ወደ ክፍሉ ዘው አልኩ። እኩለ ቀን ነው..አይነቃም ብዬ ያሰብኩበት ቀን። ሲያንኮራፋ ይሰማኛል..በዛ ውድቅት ሌሊት አባቴን ከነባርሜጣው ካገኘሁት ለዘላለም ሲገርመኝ ይኖራል እያልኩ ነበር። እናባዬ ሲተኙ በር ስለማይዘጉ በተከፈተው በር አልፌ ወደ አባዬ አቀናሁ። እንደፈራሁት ከነባርሜጣው አልነበረም። ለዘላለም በሚመስል የጊዜ ርቀት ያላየሁትን የአባቴን ራስ ያለባርሜጣ አየሁት። እውነት አልመሰለኝም..እንደ ቶማስ ካልነካሁ አላምንም ብዬ ወደ አባቴ ሌጣ ራስ ተንደረደርኩ። በራ ራሱ ብርቅ ሆኖብኝ ለመሳም በቀረበ መልኩ ተጠግቼ አየሁት። አባቴን ያለባርሜጣ አየሁት..ለመጀመሪያ ጊዜ። በአባቴ መላጣ ራስ ላይ ግን አንድ ነገር አየሁ..‹መዐዛ› የሚል ንቅሳት። አባቴ አይነቃም ብዬ ባሰብኩበትና በተሳካልኝ በዛ ውድቅት ሌሊት ሌላ ሀሳብ ሰንቄ በተደናበረ ርምጃ ወደ መኝታ ክፍሌ ተፈተለኩ። ያን ሌሊት ሳልተኛ አሳለፍኩት.. ውዬ ማደር አልቻልኩም። ሲነጋ በእንቅልፍ ጥማት የተጎለጎሉ አይኖቼን ይዤ አባቴ መላጣ ላይ ስላየሁት የሴት ስም እናቴን ልጠይቅ ድምጽዋን ወደሰማሁበት ሄድኩ። ከመቼው እንደነቃች እንጃ ማግስቱ ጾም የሆነውን በዓል በሽሮ ለማሳለፍ ጭኗ ላይ ትሪ አስቀምጣ ምስር እየለቀመች አገኘኋት። አባቴ ማታ የጠጣው የበዓል ጠላ ደብቶት ይሁን እንጃ አልተነሳም።

አይኖቼን በመዳፌ እያሻሸሁ ‹ሰናይት? አልኳት። በስሟ ነው የምጠራት።

ቀና ብላ አየችኝ..

አልተግደረደርኩም..አልተርበተበትኩም..ወዲያ ወዲህ አላልኩም ‹መዓዛ ማናት? አባዬ መላጣ ላይ..› ብዬ ሳልጨርስ እንቅልፍ ያባባው ጉንጬ ላይ አንድ ጊዜ በጥፊ ደረገመችልኝ። ሰማይ ምድሩ ዞረብኝ..ብዙ አይነት ቀለማት አንጃበቡብኝ። እናቴ እኔን ልትመታ እጇቿን ስታሰላ ጭኗ ላይ ያለው ትሪ ተደፋና ምስሩ ፈሰሰ። እሷ ወደ ምድር ስታቀረቅር እኔ የተመታ ጉንጬን ይዤ ከአጠገቧ ሸሸሁ። ሌላ ሀሳብ..ሌላ ትካዜ ተፈጠረብኝ። በስንት ጥረትና በስንት ዘመኔ የአባቴን መላጣ ባይ የእናቴ ጥፊ ትርጉሙ አልገባህ አለኝ። ያን እለት በማላውቀው ምክንያት በጥፊ መመታቴ የአባቴ መላጣ የሆነ ሚስጢር እንዳለው እንዳስብ አደረገኝ። ብዙ ቆይቼ ግን አንድ እውነት ላይ ደረስኩ። መዓዛ የአባቴ የመጀመሪያ ፍቅረኛ ነበረች። ጭንቅላቱ ላይ ስለተነቀሳት እናቴ ስለምትቀና ከእናቴ ሽሽት ባርሜጣ እንደሚያደርግ ደረስኩበት። ሌላም እውነት ላይ ደረስኩ እኔ ተወልጄም ሆነ ሳልወለድ እኛ ቤት እማዬና አባዬ የሚጣሉት አባቴ ባርሜጣ ሳያደርግ ቀርቶ እናቴ መዓዛ የሚለውን ስም ስታይ ነበር።

.........

አባቴ በዛ ባርሜጣ ከሰፈር አባቶች ሁሉ ልዩ ነው። ባርሜጣ የሌለው ራሱ እንደናፈቀኝ ዩኒቨርስቲ ገባሁ። ዩኒቨርስቲም ገብቼ የአባቴ ባርሜጣ አለቀቀኝም። ከሚያስተምሩን አምስት መምህራኖች ውስጥ ሶስቱ ባርሜጣ የሚያደርጉ ነበሩ። በጣም የሚገርመው ደግሞ ከነዛ ሶስት ባለባርሜጣዎች ውስጥ ትቸር ጋሹ የሚባሉት መምህራችን ልጄን ትመስይኛለሽ ማለታቸው ነበር። ዘወትር ክፍል በገቡ ቁጥር ‹ልጄ የታለች? ማለት ከሚወዱት ትኩስ ቡና ቀጥሎ አፋቸው ላይ የሚጠማቸው ወሬ ሆነ። እኔም አውቄ ይሁን ሳላውቅ አባትነታቸውን አምኜ መቀበል ጀመርኩ። ብዙ ነገራቸው ቤት ትቼው ከመጣሁት እውነተኛ አባቴ ጋር ይመሳሰል ነበር። እየቆየሁ ስሄድ የእውነትም አባቴን ይመስሉኝ ጀመር። በእሳቸው አባትነት እውነተኛውን አባቴን እየረሳሁት መጣሁ። በቀን አስር ጊዜ ድምጹን ካልሰማሁ ሰላም የማይሰማኝን አባቴን በሳምንት አንድ ቀን ብቻ አገኘው ጀመር። አንዳንድ ጊዜ መምህርነታቸውን ረስቼ እንደ እውነተኛ አባቴ እባጥጥባቸው ነበር።

ክፍል ውስጥ፣ ግቢ ውስጥ ሁሉም ሰው አባትና ልጅ አድርጎ ተቀበለን። በዛ ሁሉ የአባትና ልጅ ግንኙነታችን ውስጥ የጎንደር ልጅ ከመሆኔ ባለፈ አንድም ቀን ስለቤተሰቦቼ ጠይቀውኝ አያውቁም። እንኳንም አልጠየቁኝ እላለሁ። ቢጠይቁኝ ምን እላቸው ነበር? አባቴ እንደ እርሶ በባርኔጣ ተኝቶ የሚነቃ ነው። ዘመኔን ሙሉ እጁ ላይ ስቦርቅ፣ ክንዱ ላይ ስዘል ሌጣ ራሱን አይቼው አላውቅም። ዛሬ ደግሞ ቁርጥ አባቴን የሚመስሉ ርሶ ላይ ወደኩ እልላቸው ነገር።

ከአምስት ዓመት የተማሪነት ሕይወት በኋላ ተመረኩ። አመራረቁ ለኔም ለታሪኬም እንግዳ ነበር። የምርቃቴ ቀን በሁለት ባርሜጣ ባደረጉ አባቶች ተከብቤ ተመረኩ።

# ዓለም አቀፍ




## በኤሌክትሪክ የሚሠራ አውሮፕላን የመጀመሪያውን በረራ አደረገ

የእስራኤሉ ኢቪዬሽን ኩባንያ በኤሌክትሪክ የሚሠራ አውሮፕላኑን ለስምንት ደቂቃ በአየር ላይ ማብረሩ ተገለጸ። የእስራኤሉ ኢቪዬሽን ኤርክራፍት የተሰኘው ኩባንያ ሙሉ ለሙሉ በኤሌክትሪክ የሚሠራ አውሮፕላን የመጀመሪያውን በረራ በማድረግ ከአሜሪካው ዋሸንግተን ኤርፖርት በመነሳት በ3 ሺሕ 500 ጫማ ከፍታ ሁለት አብራሪዎች እና ሰባት ተሳፋሪዎችን በመያዝ የሙከራ በረራውን እንዳካሄደ ሲኤንኤን ዘግቧል።

የኩባንያው ሥራ አስኪያጅ ግሪጎሪ ዳቪስ እንዳሉት በአውሮፕላን የሞተር ኃይል ታሪክ ከ1950ዎቹ በኋላ ሲለወጥ እንዳላዩ ገልጸው ላለፉት 70 ዓመታት ታሪክ ውስጥ ሁሉም አውሮፕላኖች በነዳጅ የሚንቀሳቀሱ እንደነበሩ አስታውሰዋል። በአሁኑ ሙከራ ሙሉ ለሙሉ በኤሌክትሪክ የሚሠራ አውሮፕላን ለማምረት የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እንደሆነም አክለዋል።

የዚህን አውሮፕላን የባትሪ ቴክኖሎጂ ልክ በኤሌክትሪክ ቻርጅ ከሚሠሩት ተሽከርካሪዎች ጋር ተመሳሳይ ለማድረግ እየተሠራ እንደሆነም ተገልጿል። የአንድ አውሮፕላን ቻርጅ የማድረጊያ ጊዜን በ30 ደቂቃ ውስጥ ለማድረግ ታቅዷል የተባለ ሲሆን የአውሮፕላኑን አሁናዊ ፍጥነት በሰዓት 287 ማይል ርቀት ይጓዛልም ተብሏል።

በፈረንጆቹ 2015 ላይ የተቋቋመው ኢቪዬሽን ኩባንያ ከአራት ዓመት በኋላ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ አውሮፕላኖችን ለዓለም ገበያ የማቅረብ እቅድ አስቀምጦ ነበር። ይሁንና የኮሮና ቫይረስ እና ሌሎች የዓለም ክስተቶች በተቀመጠው ጊዜ የኤሌክትሪክ አውሮፕላኖችን አምርቶ ወደ ዓለም ገበያ ማድረስ እንዳልተቻለ ተገልጿል።

የአሜሪካ የአቪዬሽን ቁጥጥር ባለስልጣን በኤሌክትሪክ የሚሠሩ አውሮፕላኖቹን የጥራት ደረጃ እንዲገመግም እና እንዲመረቱ ፈቃድ እንዲሰጥ የማድረግ ሥራው በቅርቡ እንደሚጀምርም ተቋም አስታውቋል። ይህ አውሮፕላን የሙከራ በረራውን በስኬት አጠናቋል የተባለ ሲሆን በረራውን ጨርሶ ወደ ምድር ለማረፍ ግን የተወሰኑ ችግሮች አጋጥመዋል ተብሏል።

ከአንድ ዓመት በፊት የሙከራ በረራውን የማጠናቀቅ እቅድ የነበረው ይህ የአቪዬሽን ተቋም በመጥፎ የአየር ንብረት እና ኮሮና ቫይረስ ምክንያቶች ሥራውን ባሰበው ጊዜ መከወን እንዳልቻለ ጠቁሟል። በቀጣይ አንድ ዓመት ውስጥ የሙከራ ጊዜውን በማጠናቀቅ በአሜሪካ ባሉ ግዛቶች መካከል የአገልግሎት መስጠት ሙከራዎችን እንደሚያከናውንም አስታውቋል።

በእቃ ማጓጓዝ ሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ንግድ ድርጅቶች ከወዲሁ የኤሌክትሪክ አውሮፕላኖችን ለመግዛት ፍላጎት አሳይተዋል የተባለ ሲሆን ዲኤችኤል፣ ግሎባልኤክስ እና ሌሎችም ተቋማት ፍላጎት ካሳዩ ድርጅቶች መካከል ዋነኞቹ ናቸው መባሉን የአልዐይን መረጃ አመላክቷል።

## ምዕራባውያን በነዳጅ ማስተላለፊያዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት ሩሲያን ቢወነጅሉም ውንጀላውን አጣጥላዋለች

በነዳጅ ማስተላለፊያዎች ላይ የደረሰው ጉዳት የሩሲያ ሴራ ውጤት ነው ያሉት ምዕራባውያን ለማስተላለፊያዎች የሚያደርጉትን ጥበቃ እንደሚያጠናክሩ ገልጸዋል። በአንጻሩ ሩሲያ ውንጀላውን አጣጥላዋለች። በሁለት ዋና ዋና የነዳጅ ማስተላለፊያዎች ላይ እንደተደረገ በተጠረጠረ ሴራ ጉዳት ከደረሰ በኋላ የአውሮፓ ሀገራት ለማስተላለፊያዎቹ የሚደረገውን ጥበቃ እንጠናከራለን አሉ።

የአውሮፓ ኅብረት፥ አሜሪካ እና ኔቶ ሩሲያን በቀጥታ ባይኮንኑም ከሩሲያ ወደ ጀርመን በተዘረጋው የነዳጅ ማስተላለፊያ ላይ የደረሰው ጉዳት ሆን ተብሎ የተፈጸመ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል። ሩሲያ ጉዳዩ ላይ እጇ እንደሌለበት የገለጸች ሲሆን በምትኩ አሜሪካ ተሳትፋ እንደሆነ ጠይቃለች። ቀደም ባሉ ጊዜያት ሩሲያ ምዕራባውያኑ ለዩክሬን ድጋፍ በማሳየታቸው የጋዝ አቅርቦትን እንደጦር መሳሪያ በመጠቀም ልትጎዳቸው ትሞክራለች የሚል ወቀሳ ይቀርብባታል።

ኖርድ ስትሪም አንድ እና ሁለት በተባሉት የነዳጅ ማስተላለፊያዎች እንደሚያፈሱ የታወቀው በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ሰኞና ማክሰኞ ነበር።ሁለቱም ማስተላላፊያዎች ከስራ ውጪ ሲሆኑ ኖርድ ስትሪም 2 ሩሲያ ዩክሬንን ስትወር ከጥቅም ውጪ ሆኗል። ኖርድ ስትሪም 2 ደግሞ ለጥገና በሚል ሩሲያ በዚህ ወር ዝግ አድርጋዋለች።

ሆኖም ሁለቱም ማስተላለፊያዎች አሁን ድረስ በነዳጅ የተሞሉ ሲሆን ጉዳት የደረሰባቸው በባህር አቅራቢያ የሚገኝ እና አንድ ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ነው። የዴንማርክ የኃይል አቅርቦት ሚኒስትር ዳን ጆርጌንሰን በጉዳቱ ምክንያት እየደረሰ ያለው ፍሳሽ



ጋዙ ሙሉ በሙሉ እስኪያልቅ እና እስኪቆም ቢያንስ ሳምንት ይወስዳል ብለዋል።

የአውሮፓ ኅብረት ኮሚሽን ኃላፊ ኡርሱላ ቮን ዴር ማስተላለፊያው ላይ የደረሰው ጉዳት ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑ ከተረጋገጠ “ጠንካራ አጸፋ” ሊኖር እንደሚችል ጠቁመዋል። በሌላ በኩል የፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ቃል አቀባይ ዲሜትሪ ፔስኮቭ የማስተላለፊያው ጉዳት በሩሲያ ነው የደረሰው መባሉን አስተባብለው ክሱን ተገቢነት የሌለው ነው ሲሉ አጣጥለውታል። ፔስኮቭ ፍሳሹ “እጅግ አሳሳቢ” ነውም ብለዋል።

በማስተላላፊያዎቹ ጉዳት መድረሱ ከተሰማ በኋላ አሁን ላይ በአውሮፓ ትልቋ ነዳጅ አቅራቢ የሆነችው ኖርዌይ የማስተላለፊያ መስመሩን የሚጠብቅ ሠራዊት ለማሰማራት ወስናለች። የኔቶ የደህንነት ዘርፍ ኃላፊ ጄንስ ስቶልበርግ ጉዳቱ ከደረሰበት ስፍራ አቅራቢያ የምትገኘው ዴንማርክ የመከላከያ ሚኒስትር ጋር መምከራቸውን ገልጸዋል።

የዋይት ሃውስ ብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ጃክ ሱሊቨን የአውሮፓ ሀገራት የነዳጅ ማስተላለፊያ ደህንነቱን ለማስጠበቅ የሚያደርጉትን ጥበቃ ሊያጠናክሩ ይገባል ብለዋል።የአሜሪካ የባህር ኃይል አጋሮቹን ለማገዝ ዝግጁ ነውም ተብሏል።ኖሮድ ስትሪም 1 የነዳጅ ማስተላለፊያ ሁለት ትይዩ መስመሮች ያሉት ሲሆን 1200 ኪሎ ሜትር የሚረዝም እና በባልቲክ ባህር አቋርጦ ከፒተርስበርግ ተነስቶ ምስራቅ ጀርመን የሚደርስ መሆኑን የዘገበው ቢቢሲ ነው።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency



ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ጎፈሬ ለ17 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ትጥቅ ለማቅረብ ተስማማ

ብርሃን ፈይሳ

በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት የሚካሄደው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ(ሴካፋ) ከ17 ዓመት በታች የእግር ኳስ ዋንጫ ከነገ በስቲያ ይጀመራል። በውድድሩ ላይ የሚሳተፈው የኢትዮጵያ ከ17 ዓመት በታች ወንዶች ብሔራዊ ቡድንም ከጎፈሬ የስፖርት ትጥቅ አምራች ሙሉ የትጥቅ አቅርቦት ተደርጎለታል።

ከ17 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድኖች የአፍሪካ ዋንጫ ተሳታፊ ለመሆን በምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ እግር ኳስ ማኅበር የማጣሪያ ውድድር በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት ዘንድሮ ለ5ኛ ጊዜ ይካሄዳል። በዚህ ውድድር ላይም ስምንት ሀገራት በሁለት ምድብ ተከፍለው የሚሳተፉ ሲሆን፤ ከነገ በስቲያ መስከረም 22/2015 ዓም በአበበ ቢቂላ ስታዲየም ይጀመራል። አንድ ቀን ቀደም ብሎ ለመጀመር መርሐ ግብር ተይዞለት የነበረው ይህ ውድድር ከተጫዋቾች የእድሜ ምርመራ ጋር ተያይዞ ያላጠናቀቁ ብሔራዊ ቡድኖች በመኖራቸው አንድ ቀን ማራዘም እንዳስፈለገም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከትናት በስቲያ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አስታውቋል።

ፌዴሬሽኑ በውድድሩ ላይ ለሚሳተፈው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ሙሉ የትጥቅ አቅርቦት ከጎፈሬ የስፖርት ትጥቅ አምራች ማግኘቱንም በመግለጫው ጠቁሟል። የትጥቅ አቅርቦት ስምምነቱ ሃገር በቀል የስፖርት ትጥቅ አምራች ከሆነው ጎፈሬ ጋር ሲደረግ እንደተገለፀው፣ ለብሔራዊ ቡድኑ የስፖርት ትጥቁ በነጻ መቅረቡ



የትጥቅ አቅርቦት ስምምነቱን አቶ ባሕሩ ጥላሁንና አቶ ሳሙኤል መኮንን ተፈራርመዋል፣

የተጠቆመ ሲሆን ለ25 ተጫዋቾች የሚሆን ሶስት ዓይነት የመጫወቻ ትጥቅ፣ ሁለት የመለማመጃ፣ 10 የቴክኒክ ቡድን አባላትን እንዲሁም ሌሎችንም ያካተተ ስምምነት እንደተፈረመ ተገልጿል። በዓይነት የተደረገው ይህ ድጋፍ ወደ ገንዘብ ሲለወጥም 1ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር እንደሚያወጣም የጎፈሬ ስፖርት ትጥቅ አምራች ሥራ አስኪያጅ አቶ ሳሙኤል መኮንን ጠቁመዋል።

ከተቋሙ ጋር የስፖንሰር ሺፕ ስምምነቱን የተፈራረሙት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ባህሩ ጥላሁን በበኩላቸው፤ ስምምነቱ የሃገር ውስጥ የስፖርት ትጥቅ አምራቾችን ከማበረታታት ባለፈ ለሌሎችም መነቃቃትን የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል። ከዚህ ቀደም የልምምድ ትጥቆችን ለተለያዩ ብሔራዊ ቡድኖች እንዲሁም ክለቦች ሲያቀርብ የቆየው ጎፈሬ የተሟላና ጥራት ያለው ትጥቅ ማምረት በመጀመሩ በውድድሩ ላይ ለሚካፈለው ቡድን እንዲያቀርብ ተደርጋል። በዚህም ፌዴሬሽኑ በነጻ ትጥቅ ከማግኘቱም ባለፈ ገበያውን በአፍሪካ ሃገራትም በማስተዋወቅ ላይ ለሚገኘው ተቋም የገበያ እድል የሚፈጥር በመሆኑ በስምምነቱ ሁለቱም አካላት ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ተገልጿል።

ስምምነቱን ተከትሎ የጎፈሬ ሥራ አስኪያጅ አቶ ሳሙኤል መኮንን፤ ትጥቆቹ በጥራት የተዘጋጁ መሆናቸውን አስታውሰው፤ ከዚህ ቀደም የማይታወቅበትን ምርቶችንም ጭምር በማምረት ለዚህ ውድድር ብቻ ብሔራዊ ቡድኑን እንደሚደግፍ ተናግረዋል። ከክለቦች ጋር በስፋት እየሠራ የሚገኘው ጎፈሬ ለብሔራዊ ቡድን ሙሉ ትጥቅ ሲያቀርብ ይህ የመጀመሪያው ነው። ፌዴሬሽኑ ለሰጠው ለዚህ እድልም ሥራ አስኪያጁ ምስጋናቸውን አቅርበዋል። የተቋሙ እቅድም ምርቱን በምስራቅ አፍሪካ ሃገራት ማስተዋወቅና ማቅረብ መሆኑን ሥራ አስኪያጁ አያይዘው ገልጸዋል።

ጎፈሬ የስፖርት ትጥቅ አምራች እና የስፖርት መርሐ ግብር መሪ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ወደ ገበያው የገባ ተቋም ሲሆን፤ ከበርካታ የቤትኪንግ ኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ክለቦች ጋር ይሠራል። ከሃገር ውስጥ ለ15 ክለቦች ትጥቅ ያቀረበ ሲሆን፤ ከዚህ ባለፈም ምርቶቹን በተለያዩ የአፍሪካ ሃገራት ዩጋንዳ፣ ደቡብ ሱዳን እና ዛምቢያ በመላክም ጭምር የውጪ ምንዛሪ እያስገኘ የሚገኝ ተቋም መሆኑም በጋዜጣዊ መግለጫው ወቅት ተጠቁሟል።

ለ20 ቀናት የሚካሄደው የሴካፋ ከ17 ዓመት በታች ውድድር 10 ሃገራት ይካፈላሉ ተብሎ ቢጠበቅም 8 ብቻ እንደሚሳተፉ አረጋግጠዋል። ሃገራቱ በሁለት ምድብ ተከፍለው የሚወዳደሩ ሲሆን፤ በመጀመሪያው ምድብ አዘጋጇ ኢትዮጵያ፣ ታንዛኒያ፣ ሶማሊያ እና ደቡብ ሱዳን ተደልድለዋል። በሌላኛው ምድብ ደግሞ ዩጋንዳ፣ ጅቡቲ፣ ሱዳን እና ብሩንዲ የሚገናኙ መሆኑን መርሐ ግብሩ ያሳያል። በዚህ ውድድር ላይ ተካፋይ የሚሆኑት ሃገራትም አስቀድመው ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ ይገኛሉ።

## የጨረታ ማስታወቂያ

በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን የገላን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የተለያዩ ቋሚ፣አላቂ የፅህፈት መሳሪያዎች ፣የፅዳት ዕቃዎች የደንብ ልብስ እና የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ፣በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የምታሟሉ ህጋዊ ድርጅቶች መወዳደር ትችላላችሁ፡

1. ተጫራቾች በጨረታ ለመካፈል ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች ከ100,000 ብር ለሆነ ግዥ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ ተመዝጋቢ የሆኑና ለዚሁ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
3. በገንዘብና ትብብር ልማት ሚኒስቴር ወይም በሌላም በሚመለከታቸው ፈቃድ ሰጪ አካላት በአቅራቢነት የተመዘገቡና የምስክር ወረቀት ያላቸው ተጫራቾች ብቻ መካፈል ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች ሰነዱን ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት በነፃ መውሰድ ይችላሉ፡፡
5. ተጫራቾች በጨረታ ተካፋይ ለመሆን የሚፈልጉት ለምን ለምን ዓይነት ዕቃ እንደሆነ በሰነዶቻቸው ላይ በትክክል ለይተው መጻፍ ይኖርባቸዋል፡፡
6. ፍ/ቤቱ ካቀረበው መስፈርት /standard/በታች ማቅረብ አይቻልም፡፡
7. ማንኛውም ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ በጨረታው ሰነድ ላይ የተገለፁትን ማንኛውንም ሁኔታዎች መለወጥ ወይም ማሻሻል ወይም ጨረታውን ትቻለሁ ማለት አይችልም፡፡
8. ፍ/ቤቱ የሚያጫርታቸውን ዕቃዎች ብዛት እንደ አስፈላጊነታቸው (25%) በመጨመር ወይም በመቀነስ ማዘዝ ይችላል፡፡
9. ጨረታው የሚቆየው ለተከታታይ 10 የስራ ቀናት ይሆናል፡፡ በ10ኛው ቀን 11፡30 ተዘግቶ በነጋታው በ 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡እለቱ የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ይሆናል፡፡
10. ማንኛውም ተጫራች በጨረታ ተካፋይ ለመሆን ተመላሽ የሚሆን ባቀረበው ጠቅላላ ዋጋ ላይ 1% የጨረታ ማስከበሪያ /CPO/ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርበታል፡፡
11. ፍ/ቤቱ የተሻለ ንግድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡
12. የጨረታው ዋጋ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ መጥቀስ ይኖርበታል፡፡
13. ፍ/ቤቱ የሚያጫርታቸውን ዕቃዎች ብዛት ለተከታታይ 6 ወራት ውል ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ይዋዋላል፡፡
14. የሚገዙ ዕቃዎች በተሠጠው ስፔሲፊኬሽን መሠረት ተሞልተው ካልቀረቡና ማንኛውም ዓይነት ስህተት ቢፈፀም ሃላፊነቱ የአቅራቢው ድርጅት ነው፡፡

**አድራሻ፡-ገላን ከተማ መዘጋጃ ፊትለፊት የሚገኝ የፍርድ ቤቱ ፎቅ**
**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር ፡ 09 20 4189 05/0118871269**

**በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን የገላን**
**ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት**

## በድጋሚ የወጣ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር 03/2015

የአዳማ ጉምሩክ ኮሚሽን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሎት 1- የሆቴል አገልግሎት አዳራሽ 500 ሰው መያዝ የሚችል 300 ሰው መያዝ የሚችል እንዲሁም 100 ሰው የሚይዝ የመወያያ አዳራሽ ሶስት ያለው እንዲሁም የድምፅ ማጉያ /sound system/፣ በቂ የኢንተርኔት አገልግሎት ያለው እና ፕሮጀክተር ያለው፣ አንደኛ ደረጃ ብፌ እና ሪፍሬሽመንት በቀን ሁለት ጊዜ ግማሽ ሊትር ውሃን ጨምሮ ሁለተኛ ደረጃ ብፌ እና ሪፍሬሽመንት በቀን ሁለት ጊዜ ግማሽ ሊትር ውሃን ጨምሮ፣የአልጋ /የመኝታ/አገልግሎት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በጨረታው ለመካፈል የሚፈልጉ እና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች እንዲወዳደሩ ይጋብዛል፡፡

1. ተጫራቾች ህጋዊ የታደሰ ንግድ ፈቃድ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /Tin/ የምስክር ወረቀት ያላቸው፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት ያላቸው፣ እንዲሁም የዘመኑን ግብር የከፈሉና ግዴታቸውን የተወጡ መሆን አለባቸው፡
2. ተጫራቾች ይህ ጨረታ በማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣ ቀን ጀምሮ ለ15 ቀናት የማይመለስ ብር 100/መቶ ብር/ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን በከልቻ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር ቅጥር ግቢ በሚገኘው የአዳማ ጉምሩክ ኮሚሽን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቢሮ 31 በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
3. የጨረታ ሳጥኑ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉበት ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4:10 ታሽጎ በዛው ቀን ከጠዋቱ 4፡15 ሰዓት በግዥና ፋይናንስ ቡድን ቢሮ ይከፈታል ዕለቱ የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት የጨረታ ሳጥኑ ታሽጎ ይከፈታል
4. ማንኛውም ተጫራች ለመጫረት ያቀረበው አጠቃላይ 2% በባንክ የተመሰከረለት ቼክ /ሲፒኦ/ ወይም በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ጋራንቲ በአዳማ ጉምሩክ ኮሚሽን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስም አሰርቶ ማቅረብ አለበት ቅ/ጽ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ቢሮ ቁጥር 31**
**ስልክ ቁጥር 022-211-58-90/022-211-58-07**

**የአዳማ ጉምሩክ ኮሚሽን ቅ/ጽ/ቤት**

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ